«እግዚአብሔር ጻድቃንን ይወድዳል፤ እግዚአብሔር ስደተኞችን ይቀበላል።»
መዝ.፻፵፭፥፱

# ስምዐ ጽድቅ

## ማውጫ


፪ አጫጭር ዜናዎች
፬ መልእክት
፮ ሪፖርታዥ
፰ ቤተ አብርሃም
፲፪ ቃለ መጠይቅ
፲፭ የሕፃናት ዓምድ
፲፯ ትዝብት
፲፱ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ





ስምዐ ጽድቅ

የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በኅትመት ሚዲያ መምሪያ እየተዘጋጀ በወር ሁለት ጊዜ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ

ጳጉሜን ፫ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. ተጀመረ



☎ 011-1553555/ 011-1553442
✉ 80078
አዲስ አበባ

የዝግጅት ክፍሉ ኢሜይል
newspaper@eotcmk.org

ምክትል ዋና አዘጋጅ
ወርቅነሽ ቱፋ
ከፍተኛ ሪፖርተር
ካሣሁን ለምለሙ
ሪፖርተር
ምኒልክ ብርሃኑ
የገጽ መልክ (Layout) ዲዛይነርና
ጸሐፊ
ገነት ታደሰ



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ

# ጥልና አለመግባባትን በይቅርታና በዕርቅ መፍታት እንደሚገባ ተገለጠ

ካሳሁን ለምለሙ

ጥልና አለመግባባትን በይቅርታና በዕርቅ መፍታት እንደሚገባ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት ገለጡ፡፡

ቅዱስነታቸው ይህንን የገለጡት የ፳፻፲፮ ዓ.ም የመስቀል ደመራ በዓል አዲስ አበባ መስቀል ዐደባበይ በተከበረበት ወቅት ተገኝተው ባስተላለፉት አባታዊ መልእክት ሲሆን በመልእክታቸውም የሰው ልጆችን አለመግባባት በይቅርታና በዕርቅ ዘግቶ ሰላምና አንድነትን አስፍኖ በመከባበርና በመተሳሳብ፣በመተዛዘንና በመተ ጋገዝ፣ በመቻቻል እንዲሁም በፍቅር ከመኖር ውጭ የተሻለ ሌላ አማራጭ እንደሌለ አስገንዝበዋል፡፡

ቅዱስነታቸው አክለውም የይቅርታና የዕርቅ ሄደቱ እውን ሊሆን ሚችለው የራስ ወዳድነትን አስተሳሰብ በመተው እንደሆነ አስረድተው ከእኔ ይልቅ ለሁላችን የሚለውን አስተሳሰብ አንግቦ ሊሆን እንደሚገባም ተናግረዋል፡፡

ዕርቅና ሰላም ሊመጣ የሚችለው የጋራ መልካም አስተሳሰብ በሰዎች ልቡና የበላይነት ሲያገኝ መሆኑን የገለጡት ቅዱስነታቸው በዕርቅ ላይ የተመሠረተ የችግሮች መፍቻ መፍትሔ በፈጣሪም ሆነ በዓለማዊ ሕግ ፍጹም የሆነ ተቀባይነት ያለው መሆኑኑን አክለው አስረድተዋል፡፡

ሰዎች ጠብን በዕርቅ፣በደልን በይቅርታ፣ድኅነትን በልማት፣ ክህደትን በሃይማኖት እያረሙ መኖር እንደሚችሉ የጠቀሱት ቅዱስነታቸው ሰው ራሱን በራሱ ካላሸነፈ በስተቀር ይህንን መልካም ተግባር ለመፈጸም አቅምና ችሎታ እንደለሌውም አስገንዝበዋል፡፡

ሰላም እጅጉን ከእኛ መራቋን የተናገሩት ቅዱስነታቸው ሰላም ወደ እኛ እንድትመጣ ሁላችንም በተለይ ቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የበኩሏን ድርሻ ልትወጣ እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡

በመጨረሻም እግዚአብሔር በሀገራችን አንዳንድ አካባቢዎች ያሉ ግጭቶችን አስወግዶ ሰላም፣ፍቅር፣አንድነትንና ስምምነቱን እንዲያመጣ ሁሉም ሰው የዕርቅና የይቅርታ አካል እንዲሆን ቅዱስነታቸው ጠይቀው ለዚህ ዓላማም ሁሉም በያለበት በርትቶ እንዲጸልይ አባታዊ ጥሪ አቅርበዋል፡፡



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ኪሪል

# ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ኪሪል ከግብፅ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተወካዮች ጋር ውይይት አደረጉ

ካሳሁን ለምለሙ

የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ኪሪል ከሌሎች ብፁዓን አባቶች ጋር በመሆን ከግብፅ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተወካዮች ጋር የሁለትዮሽ ውይይት ማድረጋቸውን ኦርቶዶክስ ኮግኔት ድረ ገጽ አስነበበ፡፡

ውይይቱ የተካሄደው ሩሲያ ሞስኮ በሚገኘው መድኄዓለም ቤተ ክርስቲያን ሲሆን ውይይቱን የመሩትም በሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የአፍሪካ ጉዳዮች ተወካይ የሆኑት ሜትሮፖሊታን ልኦንድ መሆናቸውን ከዘገባው ለመረዳት ተችሏል፡፡

ቅዱስነታቸው በውይይቱ ወቅት እንደተናገሩት ከሆነ የሩሲያና የግብፅ ሕዝቦች ለረጅም ጊዜ የዘለቀው ወዳጅነት በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ጠንካራ ግንኙነት እንዲኖር ማድረጉን ተናግረው ለውይይቱ የተገኙ የግብፅ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተወካዮችን አመስግነዋል፡፡ ከዚህ በኋላ በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል የተለየና ጠንካራ ግንኙነት ለመፍጠር እንደሚሠሩም አክለው አስታውቀዋል፡፡

ቅዱስነታቸው አክለውም "ምንም እንኳን በጦርነት፣በጥፋትና በጭንቀት ውስጥ ብንሆንም በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናትና በሁለቱ ሀገራት ሕዝቦች መካከል ያለው ግንኙነት የበለጠ ይጠናከራል እንጅ አይቀዘቅዝም" ብለዋል፡፡

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በአፍሪካ ለሚገኙ አብያተ ክስቲያናት የተለየ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥታ እየሠራች መሆኑን ቅዱስነታቸው ተናግረው የኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና ሌሎች በአፍሪካ የሚገኙ አብያተ ክስቲያናትን ግንኙነት የበለጠ ለማሳደግ የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ራሱን የቻለ ማእከል ማቋቋሚን በውይይቱ ላይ አስረድተዋል፡፡

ቅዱስነታቸው አክለውም የበለጠ ግንኙነትና መግባባት እንዲኖር በምሥራቅና በኦሬንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት አስተምህሮ ላይ ውይይት እንዲደረግ በውይይቱ ጠይቀዋል፡፡ የግብፅ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተወካይ የሆኑት ሜትሮፖሊታን ስራፒዮን በበኩላቸው በውይይቱ ላይ መሳተፋቸው እንዳስደሰታቸው ገልጠው በዚህ ሰዓት የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት በፈተና ውስጥ እያለፈ መሆኑ እንዳሳዘናቸው ከገለጡ በኋላ ለቤተ ክርስቲያኗ ሙሉ ድጋፍ እንዳላቸው ተናግረዋል፡፡

ተወካዩ እያይዘውም በዩክሬን ጉዳይ የተፈጠረው ችግር በቅርቡ ሊፈታ እንደሚችል ያላቸውን እምነት ገልጠው ችግሩ በሰላማዊና በሰለጠነ መንገድ እንዲፈታም በጸሎት እንደሚያግዙ ገልጠዋል፡፡ በሩሲያና በዩክሬን መካከል በተካሄደው ጦርነት የሞቱና የተጎዱ ዜጎችን በጸሎታቸው እንደሚያስቧቸውም አክለዋል፡፡

# «አገልግሎት ስላለብን አንታክትም»

በዛሬው የጸና መሠረት ላይ እንድንቆም የትላንት አባቶቻችን ሕይወታችውን ሙሉ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ደክመዋል፡፡ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ሳይሰስቱ መልሰው በመስጠት ሥራን በእምነት ገልጠዋል፡፡ እንደዛሬው ዘመናዊ መገናኛ ባልነበረበት በዚያ ዘመን ባሕር ተሻግረው ተራራ ዞረው ቤተ ክርስቲያንን አገልግለዋል፡፡ ገዳም ገድመው፣ ቤተ ክርስቲያንን አንጸው፣ ወንጌልን ሰብከው ብዙ የቤተ ክርስቲያን ልጆችን አፍርተዋል፡፡ ቀለብ ሳይሰፈርላቸው ወንበር ዘርግተው ብዙዎችን ያፈሩ ሊቃውንቶቻችንን ሳይታክቱ በማገልገል ማን ይተካከላቸዋል?

ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን የብዙ ሺህ ዘመን ታሪክ ባለቤት ያደረጋት፣ በማይናወጽ ጽኑ መሠረት ላይ እንድትቆም ያስቻላት የትላንቶቹ ጽኑዓን አባቶች፣ እናቶች ፣ወንድሞችና እኅቶች ተጋድሎ ሳይታክቱ የመሥራታቸው ውጤት ነው፡፡ እኛ ዛሬ ያየነውንና የዳሰስነው እነርሱ ትላንት አሻግረው በእምነት አይተው ሠርተው አልፈዋል፡፡ እነርሱ ዛሬ ላይ ባይኖሩም ሥራዎቻቸው ሕያው ምስክሮች ናቸውና አፍ አውጥተው ይመሰክራሉ፡፡ ቤተ ክርስቲያን በየዘመናቱ የገጠማትን ልዩ ልዩ ፈተና በድል ልትወጣ የቻለችው ትላንት በነበሩ ሕይወትን በተግባር በተረጎሙ ልጆቿ መሆኑ ሊዘነጋ አይገባም፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ ‹‹እንግዲህ እነዚህን የሚያህሉ ምስክሮች እንደደመና በዙሪያችን ካሉልን፥ እኛ ደግሞ ሸክምን ሁሉ ቶሎም የሚከበንን ኀጢአት አስወግደን፥ የእምነታችንንም ራስ ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን፥ በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ . . .›› (ዕብ.፲፪፥፩ እና ፪) እንዳለው አስተማሪዎቻችን፣ መንገድ መሪዎቻችን፣ ምሳሌዎቻችን ብዙዎች ናቸው፡፡ ሆኖም የአባቶችን ወርቃማ አገልግሎት ከመተረክ፣ ጥቅስ ከመጥቀስ ባለፈ ስንቶቻችን በሚፈለግብን ልክ ለአገልግሎት ተግተናል?

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በአባቶቹ መንገድ የሚጓዝ፣ የእነርሱን ፈለግ የሚከተል አገልጋይ ትውልድ ትሻለችና ለዚያ ልንተጋ ይገባል፡፡

ጥቂቶች የአባቶቻቸውን ፈለግ በመከተል ቤተ ክርስቲያን ከእነርሱ የምትጠብቀውን በትጋት ሲፈጽሙ ኖረዋል፤ ዛሬም ያንን ትጋታቸውን አልተዉም፡፡ የሌሎችን በጎ አገልግሎትና ትጋት የራስ አድርጎ መውሰድ፤ በጥቂት ብርቱ አገልጋዮች ካባ ሥር ተጠልሎ የሌሎችን ብርቱ አገልግሎት እንደራስ አድርጎና ተዝናንቶ ለቀጣዩ ለዛሬው የቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ አገልግሎት አይጠቅምምና ከእንደዚህ ዓይነቱ ድንዛዜ በእውነት መውጣት ይገባል፡፡

ቅደስት ቤተ ክርስቲያን በጊዜ ቀመር የተለካ ከዓመት እስከ ዓመት የሚሠሩ ብዙ ሥራዎች አሏት፡፡ ትእዛዘ እግዚአብሔርን በተግባር በመግለጥ የመጀመሪያዋ ትምህርት ቤታችን ናትና ባሳየችን መንገድ መመላለስ ከእኛ ይጠበቃል፡፡ በቤተ ክርስቲያን፣ በቤታችን፣ በመሥሪያ ቤታችን ለአገልግሎቱ ታማኝ አድርጎ በሾመን ቦታ ላይ ሁሉ ታምነን መገኘት ከእኛ ከክርስቲያኖች ይጠበቅብናል፡፡

ለሥራ ወይም ለአገልግሎት የተሰጠውን ጊዜ እያባከኑ፤ የሥራ ወይም የአገልግሎት ጊዜ እየሸራረፉ፤ ለእግዚአብሔር የሚገባውን ለራስ እያስቀሩ፤ የማይገባቸውን እየወሰዱ፤ ከእግዚአብሔር ጊዜ ላይ ሰርቆ ለራስ እያዋሉ፡ ታምነው በተሾሙበት ከእምነት ጎድለው እየተገኙ ‹‹አገልግሎት ስላለብን አንታክትም›› በሚል መንፈሳዊ ካባ ሥር ተጠልሎ መኖር፣ በሚተጉ አገልጋዮች መሀከል አስመሳይ መሆን የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት አንድ ስንዝር ወደ ፊት አያራምድምና ከእንደዚህ ዓይነቱ ራስን የማታለል አዙሪት መውጣት ተገቢ ብቻ ሳይሆን ግዴታም ነው፡፡

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የልጆቿን ብርቱና መንፈሳዊ አገልግሎት በምትሻበት በዚህ ጊዜ እንደ ቃሉ

ታምኖ አለመገኘት፤ እንደ አንድ ክርስቲያን የድርሻን አለመወጣት ለራስ ውድቀት ለቤተ ክርስቲያንም ትልቅ ጉዳት ነውና በቤቱ ሳለን እንደሚገባን ያልሆንን ሁሉ የቤተ ክርስቲያን ዕዳ እንዳለብን ልንዘነጋው አይገባም። የትላንትናው በትጋት የተሞላ የቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ ጉዞ ዛሬን እንድንኖር አድርጎናል። ትላንት የተሻለ መንፈሳዊ አገልግሎት ባይኖር ዛሬ እኛ አሁን ባለንበት ቦታ ላይ አንገኝም ነበር። በመሆኑም በተቀበልነው ልክ እንድንሰጥ፤ በተገለገልነው ልክ እንድናገለግል፤ በተላለፈልን ልክ ለሌሎች እንድናስተላልፍ፤ ዛሬያችንን የተሻለ አድርገው ባቆዩልን ልክ ነገን የተሻለ አድርጎ ለሌሎች ለማስረከብ ከጥቅስ ያለፈ በተግባር የተገለጠ አገልግሎት ከእኛ ይጠበቃል።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በብዙ አገልግሎቶቿ ውስጥ ልጆቿን ትፈልጋለች። በፈረሰው በኩል የሚቆሙ የቁርጥ ቀን ልጆችን ትሻለች። ብዙ ሰጥታናለችና ብዙ ከእኛ ትጠብቃለች። አምና በሾመችን ቦታ ሁሉ ዛሬ ታምኖ መገኘት ክርስቲያናዊ ግዴታ መሆኑን ሁሉም ልብ ሊለው ይገባል። ይልቁንም በጀመርነው በዚህ አዲስ ዓመት የትላንት ዳተኝነታችንን በመተው፤ በቸልተኝነት፣ በማናለብኝነት፣ የጎዳነውን የእግዚአብሔር ቤት አገልግሎት በመንፈሳዊ ትጋት መካስ ይጠበቅብናል።

‹‹አገልግሎት ስላለብን አንታክትም›› የሚለው ጥቅስ ሕይወት የሚኖረው በትሑት ሰብእና፤ በብርቱ አገልግሎት ውስጥ ነውና ከተለምዶ አሠራር መውጣት አለብን። ይልቁንም ለሌሎች አርአያ ለመሆን በመንፈሳዊ አገልግሎታችን ልንበረታ ይገባል። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አምና ባስቀመጠችን ሥፍራ ታምኖ በመገኘት፣ ሳይታክቱ እግዚአብሔር እንደሚያየን አድርጎ በመሥራት ክርስቲያናዊ ግዴታችንን መወጣት አለብን።

ይልቁንም ዛሬ ቤተ ክርስቲያን በስደት፣ በመከራና በመገፋት ውስጥ ባለችበት ጊዜ ተግባራዊ ክርስትና ከሁሉም የቤተ ክርስቲያን ልጅ ይጠበቃል። በአገልጋይ ስም ተጠርቶ ሳያገለግሉ ከመኖር፤ በቤቱ ውስጥ እያሉ እንደሌሉ ከመሆን ተጠብቀን፤ የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ አገልግሎት ማስመሰል በሌለበት ትጋት መፈጸም ተገቢ ነው። የነገዋን ቤተ ክርስቲያን እና መንፈሳዊ አገልግሎት ለቀጣዩ ትውልድ ለማስረከብ ዛሬ ላይ በእውነት ተግቶ ማገልገል ከእኛ በቤቱ ውስጥ ካለነው ሁሉ ይጠበቃል እንላለን።

# ማኅበረ ቅዱሳን የተቋማዊ ለውጥ ጥናት ፕሮጀክትን አጸደቀ

እንዳለ ደምስስ

ማኅበረ ቅዱሳን የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ችግር ከጊዜ ወደ ጊዜ በከፍተኛ ሁኔታ መጨመር እና እየተወሳሰበ መምጣት እንዲሁም የአገልግሎት ከባቢ ሁኔታዎች መቀያየርን ተከትሎ የተቋማዊ ለውጥ ጥናት ፕሮጀክትን በማዘጋጀት አጸደቀ፡፡

የተቋማዊ ለውጥ ጥናት ፕሮጀክቱንም ማኅበረ ቅዱሳን የተመሠረተበትን ፴ኛ ዓመት ፲፭ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤውን ከነሐሴ ፳፪-፳፬ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም “አገልግሎት ስላለን አንታክትም” በሚል መሪ ቃል በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ አዳራሽ ሲያከናውን ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት፣ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ልዩ ልዩ የመምሪያ ኃላፊዎችና ተወካዮች፣ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶችና የማእከላት ተወካዮች በተገኙበት ተወያይቶ ለማጽደቅ ችሏል፡፡

በዚህ ጠቅላላ ጉባኤም የተቋማዊ ለውጥ ጥናት ፕሮጀክቱን ተወያይቶ ከማጽደቅ በተጨማሪ የሁለት ዓመት የሒሳብ ሪፖርት እና የማስተባበሪያዎች ሪፖርት ቀርቦ ውይይት ተካሂዶባታል፡፡

በጉባኤው መክፈቻም ብፁዕ አቡነ አብርሃም የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ የባሕር ዳርና አካባቢው ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ “ሃይማኖት እና ፍጹም ተጋድሎ” በሚል ርእስ የወንጌል ትምህርት የሰጡ ሲሆን ማኅበሩ በሚሠራው ሁለንተናዊ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚያጋጥሙትን ፈተናዎች በጽናት በመቋቋም አልፎ እዚህ እንደደረሰ ሁሉ ወደፊትም ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሚጠቅሙ ተግባራትን በፍጹም ተጋድሎ በአንድነት ሊያከናውን ይገባል” ብለዋል፡፡

ብፁዕ አቡነ አብርሃም በማኅበሩ የቀረበውንም የሁለት ዓመታት ሪፖርት ካደመጡ በኋላም ለሚቀጥለው ዓመት ደግሞ የተሻለ ሥራ ለመሥራት የሚታቀድበትና ውጤታማ አገልግሎት ሊፈጸም እንደሚችል ተስፋ ማድረጋቸውን ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም “ንቁ በሃይማኖት ጸንታችሁ ኑሩ” በሚል ርዕስ ብፁዕ አቡነ እንጦንስ የምዕራብ ሐረርጌ እና አፋር አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ትምህርት የሰጡ ሲሆን በሃይማኖት መቆም ማለት ከዚህ ዓለም በሞተ ሥጋ እስከምናልፍ ድረስ እንጂ ጊዜያዊ አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡ ለዚህም ፍቅር፣ ጥንካሬና ብርታት እንደሚያስፈልግና አገልግሎቱም ሰማያዊ ክብር የሚገኝበት ከመሆኑ አንጻር ከሁሉም ጋር ተግባብቶ ማከናወን ያስፈልጋል ሲሉ አባታዊ ምክራቸውን ለግሰዋል፡፡

ማኅበረ ቅዱሳን በቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ ከተመሠረተበት ከ፲፱፻፹፬ ዓ.ም ጀምሮ ላለፉት ፴ ዓመታት የሚያጋጥሙትን ፈተናዎች በጽናት በማለፍ አገልግሎቱን አጠናክሮ የቀጠለ ሲሆን፤ ዘመኑን የዋጀ አገልግሎት ወደፊት ማከናወን እንዲችል የተቋማዊ ለውጥ ጥናት ማስፈለጉ በጉባኤው ላይ ተገልጿል፡፡

ማኅበሩ በሁለንተናዊ አገልግሎቱ የሚፈጠሩ ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት፣ ከማኅበሩ ዕድገት ጋር የሚስማማና ለቤተ ክርስቲያን ሁለንተናዊ ለውጥ የሚጠበቅበትን ሚና መወጣት እንዲያስችለው የተቋማዊ ለውጥ ጥናት ፕሮጀክት እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ የተቋማዊ ለውጡ ጥናት ፕሮጀክትም ዐራት መሠረታዊ ዝርዝር ዓላማዎችን ይዞ መዘጋጀቱን ጥናቱ ለጉባኤው በቀረበበት ጊዜ ተገልጿል፡፡

**እነዚህም፡-** የመጀመሪያው ማኅበሩ ተቋማዊ እሳቤውን፣ ቅርጹንና የአገልግሎት ይዘት ለውጥ በማድረግ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች በመፈተሽ፣ የአገልግሎት መስጫ መንገዶችን በመመርመር እና የፋይናስ ሁኔታዎችን በጥልቀት ፈትሾ የተቋቋመለትን ዓላማ እንዲያሳካ የለውጥ ሂደቱን መትለምና መተግበር፤

ሁለተኛው ደግሞ ማኅበሩ የአገልግሎት አፈጻጸም ለውጥ ለማድረግ የአመራር ዘይቤውን፣ አደረጃጀቱን፣ የሰው ኃይሉን፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀሙን እና የአገልግሎት አፈጻጸም ሂደቱን በጥልቀት በመፈተሽ የአደጋ ተጋላጭነትን በማጥናት ሁለንተናዊ ለውጥ

የሚመጣበትን አቅጣጫ ማሳየትና ለውጡን መተግበር፤

ሦስተኛው የቤተ ክተርስቲያንን ሁለንተናዊ አገልግሎት ለማሳደግ የሚያስችል የአጋር አካላትና የተጽእኖ ፈጣሪ አካላት ጥምረት በመፍጠር ለቤተ ክህነት ተቋማዊ ለውጥ የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ፤

ማኅበሩ እስከ አሁን የሠራቸውን ሥራዎች ገምግሞ የወደፊት የትኩረት አቅጣጫዎችን በመለየት ተጠያቂነት ያለው የአመራር ሥርዓት በመዘርጋት አሠራሩንና አደረጃጀቱን ማዘመን የሚሉ ናቸው፡፡

እነዚህን የጥናት ዓላማዎች መሠረት በማድረግ አዲስና ጥርት ያለ ተቋማዊ ርእይ፣ ተልእኮ እና ዓላማ ለመቅረጽ ተቋማዊ ወሰን፣ ተቋማዊ ጠባይ፣ የተቋማዊ ዓላማ ትኩረት እና ተቋማዊ ቅርጽ አመላካች ርእሰ ጉዳዮችን በዝርዝር በመመልከት ለውሳኔ በሚመች መልኩ አጠቃልሎ በማቅረብ የቀጣዮችን ዘመናት የማኅበሩ ርእይ፣ ተልእኮና ዓላማዎች መወሰናቸውን በዝርዝር የተቋማዊ ጥናት ፕሮጀክቱ ሲቀርብ ተገልጿል፡፡

ማኅበረ ቅዱሳን ይህንን ተቋማዊ ለውጥ ለመተግበር ትኩረት ሰጥቶ የሚሠራቸውን የአገልግሎት ዘርፎች ለመምረጥ የተቀመጡ መሥፈርቶችን ስንቃኝ ደግሞ፡- የቤተ ክርስቲያንን አቅም የሚገነቡ፣ ዘላቂ፣ ተግባራዊ ኦርቶዶክሳዊነትን የሚያጸኑ፣ አስተማማኝ የቤተ ክርስቲያን ሕልውና እና ተልእኮ ማስፈጸም የሚያስችሉ፣ የዕድገት ጥራት ኖሯቸው ለማስፋትና ለማጠናከር የሚያግዙ፣ አሳታፊ አገልግሎት፣ ልማትን የሚያፋጥኑ፣ እንዲሁም አጭር እና ረጅም ጊዜያትን ያማከሉ ትውልድ ተሻጋሪ ለውጦች ናቸው፡፡

በዚህም መሠረት የማኅበረ ቅዱሳን ርእይ፣ ተልእኮና ዓላማዎች የሚከተሉት ሆነው ተቀርጸዋል፡-

- ❖ ርእይ፡- ቤተ ክርስቲያን ሁለንተናዊ የመሪነት ሚናዋን ስትወጣ ማየት፤
- ❖ ተልእኮ፡- ለቤተ ክርስቲያን ተልእኮ መሳካት እና ለህልውናዋ የሚተጋ፣ የተደራጀ፣ ምሉዕ ኦርቶዶክሳዊት፣ ርቱዕ ዘመናዊ፣ ሁለገብ መሪ ትውልድ ማፍራት እና ማሰማራት፤
- ❖ የማኅበሩ ዝርዝር ዓላማዎች፡- የቤተ ክርስቲያንን ተቋማዊ አስተዳር፣ የአሠራር ሥርዓትና አስተሳሰብ በቴክኖሎጂ እና በልዩ ልዩ መንገዶች በመደገፍ ዘመኑን የዋጀ ጠንካራ አገልግሎት ማብቃት፤
- ❖ በተደራጀና ተደራሽነትን ማእከል ባደረገ መንገድ ስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮን ዘርፈ ብዙ በሆኑ መንገዶች በመላው ዓለም ማስፋፋት፤
- ❖ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎችን ሙሉ ሰብእናን በሚገነባ ሥርዓተ ትምህርት በማስተማር ዘመኑን የዋጁ ምሉዕ ኦርቶዶክሳዊ የሆኑ በቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ መዋቅር የሚያገለግሉ እንዲሁም በማኅበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ፣ በፖለቲካዊ እና በሀገር አስተዳር ጉዳዮች መሪ/ንቁ ተሳታፊ አገልጋዮችን ማፍራት እና ማሰማራት፤
- ❖ በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚነዙትን የርእዮተ ዓለም፣ የሐሰት ትርክቶች እና የአጽራረ ቤተ ክርስቲያንን እንቅስቃሴን በጥናት እና ምርምር ላይ ተመርኩዞ መሞገት እና የተሳሳቱትን በማረም በጠንካራ የዕቅበተ እምነት አገልግሎት የቤተ ክርስቲያንን ህልውና ማስጠበቅ፤
- ❖ የተተኪውን ትውልድ መሠረት ለማጎልበት የሰንበት ትምህርት ቤቶችን አቅም በማጠናከር የሕፃናት እና የወጣቶች የተተኪነት ሚና ማሳደግ፤
- ❖ ማኅበሩ ዘመኑን የዋጀ ተቋማዊ የአሥራር ሥርዓት በመዘርጋት ተልእኮውን ማሳካት የሚችልበት አቅም መፍጠር (በአመራር፣ በሰው ኃይል፣ በመንፈሳዊነት፣ በግንኙነት፣ በዕውቀት፣ በልማት፣ በፋይናንስ፣ በቴኖሎጂ)
- ❖ ዓለም አቀፍ ግንኙነትንና የትብብር አገልግሎትን መርህ ያደረገ የኦርቶዶክሳውያንን ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ተሳትፎ ማሳደግ፡፡

እነዚህንና ሌሎችን ዓላማዎች መሠረት በማድረግ የአገልግሎት አድማሱን በማስፋትና በማጠናከር መፈጸም እንዲችል ይህ የተቋማዊ ለውጥ ጥናት ፕሮጀክት ይፋ መደረጉ ለጉባኤው ተገልጿል፡፡

ጉባኤውም በቀረበው የተቋማዊ ለውጥ ጥናት ፕሮጀክት ላይ ለአንድ ቀን ሙሉ ትኩረት ሰጥቶ ሲወያይ ከቆየ በኋላ እንዲጸድቅ ተደርጓል፡፡

ከተቋማዊ ለውጡ ጥናት ፕሮጀክት በተጨማሪ ማኅበረ ቅዱሳን ባለው መዋቅር መሠረት እያንዳንዱ የአገልግሎት ማስተባበሪያ ተስፍሮና ተለክቶ የተሰጠውን አገልግሎት

ለማከናወን የተደረጉ ጥረቶች፣ በአገልግሎት ላይ የነበሩ መልካም ዕድሎች፣ እንዲሁም ያጋጠሙ ችግሮችና ስጋቶችን ያካተተ ሪፖርት በየማስተባበሪያ ኃላፊዎች ቀርቦ ውይይት ተካሂዶባቸዋል፡፡

የተቋማዊ ለውጥ ጥናት ፕሮጀክቱ መጽደቁ እንደ መልካም አጋጣሚ መመልከት ይቻላል፡፡ ይህም ማኅበሩ አገልግሎቱን እንዲፈትሽ ያደርገዋልና፡፡ ነገር ግን ከመተግበሩ በፊት ማኅበረ ቅዱሳን ባሳለፈው የአገልግሎት ጉዞ ሲያጋጥሙት የነበሩ ችግሮችን መለየት እና ለችግሮቹ መፍትሔ መሻት ያስፈልጋል፡፡ በተለይም ለአገልግሎት እንቅፋት ሆነው የቆዩትን ከተለያዩ አካላት ያጋጥሙ የነበሩ አለመግባባቶችን ለመፍታት ትኩረት መስጠት ይገባል፡፡ አገልግሎት በመግባባትና በፍቅር የሚከናወን ነውና፡፡

አንዳንድ አካላት በተለይም መንግሥት በተለወጠ ቍጥር ከሚከተለው ርእዮተ ዓለም አንጻር ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን ጋር ተቀራርቦ ከመሥራት ይልቅ በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ ያነጣጠረ የመግፋት ብሎም የማጥቃት ሴራ ሲሠራባት ቆይቷል፡፡ በዚህም መሠረት ለቤተ ክርስቲያን ጠበቃነቱን የሚገልጸውንና ለዚህም ዓላማ በቆራጥነት የሚያገለግለውን ማኅበረ ቅዱሳንን በተለያዩ መንገዶች ለማዳከም የሚሠራው ክፋት አዘል ሴራ አገልግሎቱን በተፈለገው መጠን ለማከናወን እንቅፋት ሆኖ ቆይቷል፡፡ የማኅበረ ቅዱሳን አባላትም "ፖለቲካን በሩቁ" በሚል አካሄድ መሸሻቸው መንግሥትና በመንግሥት አስተዳደር ውስጥ ተሰግስገው ያሉ አካላት በቤተ ክርስቲያን ላይ አሉታዊ ረጅም እጃቸውን እንዲያሳርፉ ዕድል ሰጥቶቷቸዋል፡፡ ቤተ ክርስቲያንና ማኅበረ ቅዱሳንን ለመለያየትም ብዙ ደክመዋል፡፡

ለዚህ ችግር ቤተ ክህነትም ሆነ ማኅበሩ መቋቋም የሚችሉበትን አቅም መፍጠር፣ እርስ በእርስ ከመገፋፋት ይልቅ በጋራ ለመሥራት፣ ብሎም በመንግሥት አስተዳደር ውስጥ ለቤተ ክርስቲያን የሚቆም ትውልድ መፍጠር ይገባል፡፡ በዚህ ሂደት የማኅበረ ቅዱሳን ተቋማዊ ለውጥ ችግር ፈቺ ሆኖ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

ሌላው የአጽራረ ቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴን ለመግታት እንዲሁም ምእመናንን ከሐሰተኛ መምህራንና አስተምህሮአቸው ለመጠበቅ ከዚህ ቀደም ብዙ ተደክሟል፡፡ በዚህም መልካም ውጤት ማምጣት ቢቻልም የሚፈለገውን ያህል ማኅበሩም ሆነ ቤተ ክህነት ተጉዘዋል ለማለት አያስደፍርም፡፡ ለዚህም ማሳያ የሚሆነው በየጊዜው በአጽራረ ቤተ ክርስቲያን የሚነጠቁ ግራ ቀኛቸውን መለየት የተሳናቸው ምእመናን ቍጥር ከፍተኛ መሆን አሳሳቢ ያደርገዋል፡፡ በየዓመቱ በሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ላይ የሚቀርቡ ሪፖርቶች የሚያሳዩት ይህንን ነው፡፡ ስለዚህ ነባራዊውን ሁኔታ በመረዳት እና ልዩ ልዩ ስልቶችን በመቀየስ ነፍሳትን የማዳንና የማጽናት ሥራ ላይ ብዙ መሥራት ያስፈልጋል፡፡

ሌላው ማኅበረ ቅዱሳን ትኩረት አድርጎ መፈተሽ ያለበት የተቋማዊ ለውጥ ጥናቱን በታቀደለት መሠረት ውጤታማ አገልግሎት ለማበርከት የሚያስችለው መሆኑን በመገምገም ቀደም ተከተሎችን በማውጣት ዘመኑን የዋጀ አገልግሎት ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን መስጠት ይጠበቅበታል፡፡ በወረቀት ላይ የሰፈረውን ወደ ተግባር ለመለወጥ ስልታዊ ዕቅዶችን በመንደፍ አገልጋዮችን ማሠማራት፣ ሥራን ሰፍሮና ለክቶ መስጠትና መከታታልን፣ በዚያው መጠን ደግም የሚያጋጥሙ ችግሮችን መፍታት ይገባል፡፡

በዚህም መሠረት ማኅበረ ቅዱሳን በአገልግሎት ባለፈባቸው ፴ ዘመናት ያጋጠሙትን ችግሮች፣ ችግሮቹንም ለመፍታት ያደረጋቸውን ጥረቶችና የተገኙት ውጤቶችን በመገንዘብ፣ በመመርመርና በመተንነተን ጊዜውን የዋጀ አገልግሎት ለመፈጸም የተቋማዊ ለውጥ ጥናቱ ጊዜውን የጠበቀ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንና ሀገራችን እንዲሁም ዓለም ያሉበትን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ እንደመዘጋጀቱ ከበፊት ይልቅ መትጋትን፣ ከሌሎች አጋር አካላት ጋር ተቀራርቦ መሥራትና የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ህልውና ማስጠበቅ ስለሚገባ ሁሉም ሊረባረብ ይገባል፡፡ ተቋማዊ ለውጥ ማደረግ ብቻ ሳይሆን ለአገልግሎቱ ምቹ ከባቢያዊ ሁኔታዎችንም ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡


ማኅበረ ቅዱሳን በእግዚአብሔር ፈቃድ በቅዱስ ሲኖዶስ ሕጋዊ ዕውቅና ተሰጥቶት ከተመሠረተበት ከ፲፱፻፹፬ ዓ.ም ጀምሮ መዋቅሩን በሀገር ውስጥ እና በመላው ዓለም በመዘርጋት አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ በዚህም አገልግሎቱ በሀገር ውስጥ፡- ፶ ማእከላት፣ ፬፻፵፬ ወረዳ ማእከላት፣ ፩፻፲፬ የግንኙነት ጣቢያዎች እና ፬፻፳፯ ግቢ ጉባኤያት አሉት፡፡ እንዲሁም በውጪ ሀገራት ስድስት ማእከላት፣ ፳፬ ንዑሳን ማእከላት፣ ፳፮ ግንኙነት ጣቢያዎች እና ፲፰ ግቢ ጉባኤያት አሉት፡፡ ከ፶ ሺህ በላይ አባላት፣ ከ፲፫፻፶፪ በላይ መደበኛ አገልጋዮች እና በሚሊዮን የሚቆጠሩ ደጋፊ ምእመናን በመያዝ ላለፉት ፴ ዓመታት መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎቶችን አከናውኗል፡፡

# ልዩ በሆነው የሥነ ጹሑፍ ችሎታቸው ስብከተ ወንጌልን ሲያስተምሩ የነበሩ አባት

ካሳሁን ለምለሙ

ክፍል አንድ

መጋቤ ምሥጢር ወልደ ሩፋኤል ፈታሒ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት በሚገባ ጠንቅቀው የተማሩና በተማሩት ትምህርትም ቤተ ክርስቲያንንና ምእመናንን በተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች ውስጥ ተሠማርተው ሲያገለግሉ የነበሩ አባት ነበሩ፡፡ እንዲሁም መንፈሳዊ ዕወቀታቸውንና የሥነ ጹሑፍ ችሎታቸውን ተጠቅመው በጋዜጣና በቃል ስብከተ ወንጌልን በተለያዩ አካባቢዎች ተዘዋውረው በትጋት አገልግለዋል፡፡ በተለይ በኅትመት ሚዲያው ዘርፍ ያበረከቱት አስተዋጽኦ ከፍተኛና የቤተ ክርስቲያን የኅትመት ሚዲያ ደረጃን ከፍ ያደረገ ነው፡፡ በመሆኑም መጋቤ ምሥጢር ወልደ ሩፋኤል ፈታሒን የዚህ ወር ዕትማችን የቤተ አብርሃም እንግዳ አድርገናቸዋል፡፡ በዚህ ጽሑፍም ልደታቸውን፣ የትምህርትና የአገልግሎት ጊዜያቸውን ቃኝተናል፤መልካም ንባብ፡፡



መጋቤ ምሥጢር ወልደ ሩፋኤል ፈታሒ

## ሀ. ልደትና የትምህርት ሕይወት

ክቡር መጋቤ ምሥጢር ወልደ ሩፋኤል ፈታሒ በድሮው አጠራር በወሎ ጠቅላይ ግዛት በየጁ አውራጃ ጎብሩ ወረዳ ልዩ ስሙ ዳኅና ማርያም አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ታዋቂ ከሆኑት ሊቅ አባታቸው ከአለቃ ፈታሒ ወልደ ማርያምና ከእናታቸው ከወይዘሮ አበበች ያዘው ሐምሌ ፳፬ ቀን ፲፱፻፳፰ ዓ.ም ተወለዱ፡፡ በተወለዱ በ፵ ቀናቸው ጳጉሜን ፫ ቀን ሀብተ ወልድና ስመ ክርስትና ሲፈጸምላቸው ወልደ ሩፋኤል የሚል ስም ተሰይሞላቸዋል፡፡ ከዚያም ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ንባብንና ጽሕፈትን ተምረው ዳዊት ከወላጅ አባታቸው (ከአለቃ ፈታሒ ወልደማርያም) በመማር የቃል ትምህርትን ካጠናቀቁ በኋላ የባሕረ ሐሳብ ወይም የዘመናት ማውጫ (መቁጠሪያ) ትምህርትን ከወላጅ አባታቸው አለቃ ፈታሒ ወልደ ማርያም ዘንድ ተምረው አጠናቀዋል፡፡

ትምህርታቸውን ለመቀጠል የነበራቸው ፍላጎት ከፍተኛ በመሆኑ መምህራቸውና ወላጅ አባታቸው ከሆኑት አለቃ ፈታሒ ወልደ ማርያምና በወቅቱ ከነበሩት ሌላ መምህር ዘንድ ፈቃድ ጠይቀው በርካታ የአብነት መምህራን ወደሚገኙበትና መንፈሳዊ ትምህርት በስፋት ወደሚሰጥበት ሰሜን ወሎ ወደ ሚገኘው ታላቁ የመርጦ ኢየሱስ ደብር በማቅናት ከታወቁት የድጓ ሊቅ ከሆኑት ከየኔታ ሐዋዝ ዘንድ የቃል ትምህርታቸውን አጠናክረው ተምረዋል፡፡

ከዚያ በኋላም ለምርምርና ለፍልስፍና የሚያበቃቸውን ከፍተኛውን የቅኔ ትምህርት ለመማር በነበራቸው ከፍተኛ ፍላጎት የወሎ ክፍለ ሀገር ርእሰ ከተማ በሆነችው ደሴ ርእሰ አድባራት ደብረ መድኃኒት መድኃኔ ዓለም ደብር የቅኔ ጉባኤ ቤት ወንበር ዘርግተው ያስተምሩ ከነበሩት ከየኔታ ኃይለ ማርያም ጉባኤ ቤት በመግባት ለተወሰነ ጊዜ ከተማሩ በኋላ እንደገና ወደ ታወቀችውና ግማደ መስቀሉ በእንግድነት ወደአረፈባት የጁ አውራጃ ውስጥ ወደ ምትገኘው ገነተ ልዑል ማርያም ቤተ ክርስቲያን በማምራት ጉባኤ ዘርግተው ያስተምሩ ከነበሩት የኔታ

ቂርቆስ የቅኔ ጉባኤ ቤት ገብተው ቅኔ ተቀኝተዋል፡፡ ምንም እንኳን የወላጅ አባታቸውን ያህል የተሟላ ሙያ ባይኖራቸውም ትምህርታቸውን ለማሳደግና በመንፈሳዊ ዕውቀት የተሟላ ሰው ለመሆን ከፍተኛ ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ በመቀጠልም የቅኔ ትምህርታቸውን ለማጠናከር በነበራቸው ዕቅድ በድሮ አጠራሩ በየጁ አውራጃ ደቦት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ወንበር ዘርግተው ጉባኤ አስፍተው የቅኔ ትምህርት ያስተምሩ ከነበሩት ከመምህር የኔታ ገበየሁ ዘንድ ትምህርታቸውን በሚገባ ተከታትለው ተመርቀዋል፡፡

ከዚያም ወደላስታ አውራጃ ተጉዘው በኩልመስክ ደብረ ፀሐይ ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን የቅኔ ትምህርት ያስተምሩ ከነበሩትና በተለይ በአማርኛ ቅኔያቸው ይታወቁ ከነበሩት መምህር ወልደ ትንሣኤ አካሌ ዘንድ የቅኔ አገባብ ቀጽለዋል፡፡ በዚሁ የቅኔ ጉባኤ ቤት የቅኔ ትምህርታቸውን አገባባቸውን በሚገባ አጠናክረው በመማር ለሦስጠኛ ጊዜ እስከ ዘረፋና ማስነገር በመድረስ ለመምህርነት በሚያበቃ ሁኔታ ተመርቀዋል፡፡ ይህንኑ የቅኔ ትምህርት የበለጠ ለማጠናከር በነበራቸው ከፍተኛ ፍላጎትም በምዕራብ ሐረርጌ ክፍለ ሀገር ወደ ታላቁ ደብረ ወገግ አሰቦት የአንድነት ገዳም አምርተው የኔታ ቃለ ማዕነቅ ዘንድ ተምረዋል፡፡ በዚሁ ገዳም የቅኔ አገባብ ከመቀጸላቸው በተጨማሪ የተማሪዎች አስነጋሪና ዘራፊ ሆነው ለትንሽ ጊዜ ሲያስነግሩ ከቆዩ በኋላ ለሦስተኛ በመምህርነት ተመርቀዋል፡፡ በጉባኤ ቤቱ በቆዩበትም ወቅት በሰፊው የቀጸሉትን የሊቀ ኅሩያን ዘገየን አምስት መቶ የቅኔ ዓይነት መንገድ አስፈቅደው ጽፈዋል፡፡

ከዚያ በኋላም ስለ ቅኔ ትምህርት ስፋትና ጥልቀት ከታወቁ መምህራን ጋር ከፍተኛ የሆነ ጥናትና ምርምር አድርገዋል፡፡ ከታዋቂ የቅኔ መምህራን መካከል አንዱ ከሆኑትና የቅኔን ይትበሃልና ሙያ ጠንቅቀው ከሚያውቁት የደሴ ገነተ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይና በግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ የግእዝ መምህር ከነበሩት ከአለቃ ይኩኖ አምላክ ዘንድም የየኔታ ቡሩኬን የቅኔ መንገድ፣ የጥንቱን የቅኔ ይትበሃልና መንገድ በስፋትና በጥልቀት ተምረዋል፡፡

በተጨማሪም በአጭሩ የማይገታ ከፍተኛ የሆነ የትምህርት ፍላጎት ስለነበራቸው የትርጓሜ መጻሕፍት ትምህርት ለመማር በርካታ ሊቃነ ጳጳሳትና ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ተምረው ለቁም ነገር ወደበቁበት ወደ ዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ታዕካ ነገሥት በዓታ ለማርያም ገዳም የካህናት ማሠልጠኛ አምርተዋል፡፡ ከዚህ በፊትም በደብረ ወገግ አሰቦት ቅድስት ሥላሴ ገዳም ቅኔ በሚማሩበት ወቅት ማታ ማታ ቅኔ እየተማሩ ቀን ቀን ደግሞ የገዳሙ መጻሕፍተ ብሉያት ትርጓሜ መምህር ከነበሩት ከመምህር መልአኩ ዘንድ የመጽሐፈ ነገሥትን ትርጓሜ ተምረዋል፡፡ ከዚያ በመቀጠል በሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ አዳሪ ትምህርት ቤት ገብተው ከታዋቂው የመጻሕፍተ ሐዲሳት ትርጓሜ መምህር ከሆኑት ከመምህር ገብረ ማርያም ዓለሙ ዘንድ ከዘመናዊ ትምህርታቸው ጎን ለጎን የመጻሕፍተ ሐዲሳትን ትርጓሜ ጠንቅቀው ተምረዋል፡፡ ከነበራቸው ከፍተኛ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት በተጨማሪ ሁለገብ ሰው ለመሆን በማሰብ በአማኑኤል ባብቲስት ቤተ ክርስቲያን ዘመናዊ ትምህርት ቤት ገብተው የማታ ትምህርት በመማር የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በሚገባ ተከታትለው አጠናቀዋል፡፡

በሥነ ጽሑፍና ድርሰት ችሎታቸው ለሁለተኛ ጊዜ የዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ሆነው አገልግሎት በመስጠት ላይ እያሉ ቤተ ክርስቲያኗ የረጅም ጊዜ አገልግሎታቸውን እና የሙያ ብቃታቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት በ፲፱፻፳፪ ዓ.ም ከሌሎች የቤተ ክርስቲያን ደቀ መዛሙርት ጋር በመሆን ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ራሽያ ተልከው በራሽያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በሌኒንግራድ መንፈሳዊ ኮሌጅ ከፍተኛውን የነገረ መለኮት ትምህርት በሚገባ በመከታተል ተምረዋል፡፡ በዚያም ወቅት ኮሌጁ የሥነ ጽሑፍና የድርሰት ችሎታቸውን ተመልክቶ በራሻያ ቋንቋ የሥነ ጽሑፍና የድርሰት ትምህርትን እንዲከታተሉ በመፍቀድ ትመህርታቸውን ተከታትለው ተመርቀዋል፡፡

**ለ. የአገልግሎት ሕይወት፡-**

በዚያ መልኩ መንፈሳዊና ዘመናዊ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀው ከጨረሱ በኋላ ያላቸውን መንፈሳዊና ዘመናዊ ዕውቀት ተጠቅመው አገልግሎት ለመጀመር የሚያበቃቸውን በጠቅላይ ቤተ ክህነት ትምህርትና ሥልጠና መምሪያ በኩል የተሰጠውን ፈተና አልፈው ጥር ፳፰ ቀን ፲፱፻፵፯ ዓ.ም በተጻፈ የሥራ ምደባ ደብዳቤ በመጀመሪያ በኢሉባቡር ሀገረ ስብከት በሰባኬ ወንጌልነት ተመድበው ለሁለት ዓመታት

አገልግለዋል፡፡ ከዚያም ወደ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ተመልሰው ባላቸው ልዩ የሆነ የቅኔና የሥነ ጽሑፍ ችሎታ ጥር ፱ ቀን ፲፱፻፶፰ ዓ.ም በተጻፈ የሥራ ምደባ ደብዳቤ ያን ጊዜ በቤተ ክርስቲያን እየተዘጋጀ ‹‹በማስታወቂያና መርሐ ብሔር ሚኒስትር›› በሬዲዮ ይሰጥ ለነበረው መንፈሳዊ ትምህርት አዘጋጅና የዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ ሪፖርተር በመሆን ሲያገለግሉ ቆይተዋል፡፡ ከዚያ በኋላም ታኅሣሥ ፪ ቀን ፲፱፻፷፫ ዓ.ም በተጻፈ የሥራ ምደባ ደብዳቤ በዚያው በጠቅላይ ቤተክህነት የሥነ ጽሑፍ ክፍል ኃላፊና በየሳምንቱ ለሚታተመው ዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ አዘጋጅ ሆነው እንዲያገለግሉ ተመድበዋል፡፡

በድጋሚ ታኅሣሥ ፩ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም የዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ በመሆን ፍጹም በሆነ ታታሪነትና መንፈሳዊነት አገልግለዋል፡፡ በቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ዘመናቸው ውስጥ ከገጠሟቸውና በትዕግሥት ካሳለፏቸው ፈተናዎች መካከል በየዓመቱ ጥር ወር የሚከበረውን በዓለ ጥምቀት ምክንያት በማድረግ ጥር ፲፩ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም በጅማ ከተማ በሶጦ ሜዳ በተከበረው የጥምቀት በዓል ላይ ተገኝተው ወንጌል በሰበኩበት ወቅት "ሶሻሊዝምን ነቅፈህ አስተምረሃል" ተብለው በመከሰሳቸው ያለምንም ጥፋታቸው ለአምስት ወራት ያህል ታስረው ከቆዩ በኋላ ዐቃቤ ሕግ የቀረበባቸውን ክስ ውድቅ በማድረጉ በነጻ ተፈትተው ወደ አገልግሎታቸው ተመልሰዋል፡፡

ከራሽያ መልስም ታኅሣሥ ፱ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ.ም የስብከትና ማስታወቂያ መምሪያ ኃላፊ በመሆን ተመድበው እስከ ግንቦት ፲፩ ቀን ፲፱፻፸፫ ዓ.ም ድረስ አገልግለዋል፡፡ ከዚህ ሥራ በተጨማሪም በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ መሠረት በልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን የካህናት ማሠልጠኛዎች፣ የሰበካ ጉባኤና የሰንበት ትምህርትቤቶች ማስተባበርያ ኃላፊ በመሆንም አገልግለዋል፡፡ በዚሁ አገልግሎት ላይ እያሉ የጎንደር ክፍለ ሀገር ሀገረ ስብከት ጽሕፈት ቤት ለሀገረ ስብከቱ ላበረከቱት መንፈሳዊ አገልግሎት፣ ለቤተ ክርስቲያን ለውጥና በምእመናን ማኅበራዊ አገልግሎት ላይ አዘውትረው በመሥራታቸው እና ያላቸውን የሥነ ጽሑፍ ተሰጥዖና ዕውቀት ተጠቅመው ላበረከቱት ከፍተኛ አስተዋጽኦ የአፄ ፋሲለደስ ግንብ ምስል ያለበት ከብር ቅብ የተሠራ ሽልማት በጎድ መልአኩ ተፈራ ወኪል በአቶ ዘመነ ካሣ እጅ ሽልማት በክብር ተበርክቶላቸዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ከያዙት ሥራ ላይ ደርበው በስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ የማስታወቂያ ዋና ክፍል ኃላፊ በመሆን አገልግለዋል፡፡ እንዲሁም ከመጋቢት ፲፰ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ.ም ጀምሮ በልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን መምሪያ ረዳት አስተባባሪና የሕዝብ ግንኙነት መኮንን በመሆንም አገልግለዋል፡፡ በተጨማሪ የማኅደረ ስብሐት ቅድስት ልደታና መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን በስብከተ ወንጌል አገልግሎት እንዲሳተፉ በቅዱስ ፓትርያርኩ ዘንድ ስለተፈቀደላቸው የወንጌል አገልግሎት በመስጠት አገልግለዋል፡፡ እንዲሁም በያዙት የሥራ መደብ ላይ በተጨማሪ የሥነ ጽሕፈት የበላይ ኃላፊ በመሆን አገልግለዋል፡፡

መጋቤ ምሥጢር ወልደ ሩፋኤል ፈታሒ በረጅም ጊዜ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎታቸው በአሜሪካ፣ በራሽያ፣ በደቡብ አፍሪካ፣ በናይሮቢ፣ በግብጽ፣ በሶርያ፣ በሊባኖስ በአረብ ኢምሬቶችና በመላው ኢትዮጵያ በሚገኙ አህጉረ ስብከት በአካል በመገኘት ሰፊ የሆነ የስብከተ ወንጌል አገልግሎት የሰጡ ታላቅ የቤተ ክርስቲያናችን ሊቅ ነበሩ፡፡ መጋቤ ምሥጢር ወልደ ሩፋኤል ፈታሒ ያላቸውን ከፍተኛ የሥነ ጽሑፍ ችሎታ ተጠቅመው በኃላፊነት በሚያዘጋጁት ዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ አማካኝነት ቃለ እግዚአብሔርን ለበርካታ ዓመታት አስተምረዋል፡፡ የቤተ ክርስቲያንን መልእክት በጽሑፋቸው አስተላልፈዋል፤ ጠንካራ፣ ገላጭና ተቋም ተኮር ምክረ ሐሳብ በማቅረብም ለቤተ ክርስቲያናቸው በሙያቸው ጥብቅና የቆሙ ሊቅ ነበሩ፡፡ ከልጅነት እስከ ዕውቀት ቤተ ክርስቲያን ባስተማረቻቸው ትምህርት ሲያገለግሉ ከኖሩ በኋላ ባደረባቸው ሕመም በሕክምና ሲረዱ ቆይተው ከዚህ ዓለም ድካም ዐርፈዋል፡፡ ብፁዕዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት፣ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን፣ ቤተሰቦቻቸውና ወዳጅ ዘመዶቻቸው እንዲሁም የሥራ ባልደረቦቻቸው በተገኙበት ጳጉሜን ፫ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ሥርዓተ ቀብራቸው ተፈጽሟል፡፡

# ማእከላት ለቤተ ክርስቲያን አሳቢያን ተቆርቋሪ የሆኑ ወጣቶችን አፍርተዋል

*ክፍል ሁለት*

ካሣሁን ለምለሙ

ከላይ ከተጠቀሱት ለማእከላት አገልግሎት ፈተና ከሆኑ ምክንያቶች በተለየ ሁኔታ የማኅበረ ቅዱሳንን አገልግሎትና ዓላማ ያልተረዱ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን አካላት የሚፈጥሩት ችግር ለማእከላት አገልግሎት መጠናከር ተግዳሮት ሲሆኑ ይስተዋላል፡፡ ይህ በመሆኑም ማኅበረ ቅዱሳን በማእከላት በኩል የሚያስፈጽማቸው አገልግሎቶች በተፈለገው መንገድ ሊሄዱ አልቻሉም፡፡ በማእከላት አገልግሎት ላይ እንቅፋት ለሚሆኑ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን አካላት የማኅበረ ቅዱሳንን የአገልግሎት ዓላማ በተደጋጋሚ በማስረዳት ግንዛቤ ለማስጨበት ቢሞከርም እንዚህ አካላት የራሳቸው ዓላማ ያላቸው በመሆኑ ከክፉ ድርጊታቸው ሊታቀቡ አልቻሉም፡፡ በራሳቸው ዓላማ የሚሠሩ በመሆኑ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች በሙሉ ለውጥ አላመጡም፡፡ ጥቂቶች የማኅበሩን ዓለማ ተረድተው ከጥፋት ድርጊታቸው የተመለሱ ሲሆኑ ሌሎች ግን በጥፋታቸው እንደቀጠሉ ናቸው፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- ማእከላት ከሚሰጡት አገልግሎት አንጻር ቤተ ክርስቲያንና ምእመናን ምን ተጠቀሙ ማለት እንችላለን?**

**ዲያቆን አስቻለሁ ጥላሁን፡-** የማእከላት አስተዋጽኦ ሲታሰብ ማኅበረ ቅዱሳን ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ እያደረገ ያለውን ተጋድሎ ይታሰባል፡፡ በዚህ ሁኔታ ማእከላት ለቤተ ክርስቲያንና ለምእመናን እያበረከቱ ያለው አስተዋጽኦ ተዘርዝሮ የሚልቅ አይደለም፡፡ የመጀመሪያውና ዋናው ነገር ከዚህ ቀደም የቅደስት ቤተ ክርስቲያን አባል ያልሆኑ ኢ-አማንያን እንዲሁም አሕዛብ ወገኖች አምነው፣ተምረውና ተጠምቀው የሥላሴ ልጅነትን እንዲያገኙና የቤተ ክርስቲያናችን አባላት እንዲሆኑ ማእከላት አድረገዋል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ አብነት ትምህርት ቤቶች በከፍተኛ ሁኔታ እንዲጠናከሩ አድርገዋል፡፡ አብነት ትምህርት ቤቶች በመጠናከራቸው ደግሞ የነገዋን ቤተ ክርስቲያን የሚረከቡ በርካታ ሊቃውንትን ማፍራት ተችሏል፡፡ ጉባኤ ቤቶቻችን ከመጠናከራቸው በተጨማሪ የተለየ ትኩረት እንዲያገኙ አግዘዋል፡፡ ማኅበሩ በፈጠረው ግንዛቤ የጉባኤ ቤቶች ጥቅም በደንብ እንዲታወቅ ሆኗል፡፡

እንደሚታወቀው ማኅበረ ቅዱሳን የተለያዩ መገናኛ



ዲያቆን አስቻለሁ ጥላሁን

ብዙኃንን ጨምሮ በተለያዩ መንገዶች ስብከተ ወንጌልን ለምእመናን ያደረሰና እያስፋፋ ቆይቷል፡፡ ይህ በመሆኑም ምእመናንም ሆኑ ኢ-አማንያን ቤተ ክርስቲያንና ሥርዓቷን በሚገባ እንዲያውቁ አድርጓል፡፡ በተሠራው ሥራ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎትና ነገር ያገባኛል የሚሉ ወጣት ኦርቶዶክሰውያን እንዲፈጠሩ ማእከላት ከፍተኛ ድርሻ አላቸው፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን ከተመሠረተበት ጊዜ አንስቶ የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ሊደግፉ የሚችሉ በሁለት ጎን የተሳሉ

እንቁና ብቁ የግቢ ጉባኤያት ተማሪዎችን ማስመረቅ ችሏል፡፡ የተመረቁትም በተለያዩ የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ዘርፎች ተሳታፊ እየሆኑ ይገኛሉ፡፡ ወጣቱ ትውልድ ሃይማኖቱን ጠንቅቆ በማወቅ ከሱስ፣ ከኃጢያት፣ ከስርቆት፣ጊዜን በአለባሌ ቦታ ከማሳለፍና ከመሳሰሉት ጎጂ ድርጊቶች እንዲቆጠብ ሆኗል፡፡ ወጣቶች ለሥጋና ለነብሳቸው የሚጠቅማቸውን ለይተው መረዳታቸው በመልካም ሥራ እግዚአብሔርን ከማስደሰት ባሻገር ለቤተሰቦቻቸው ከፍተኛ የአዕምሮ ረፍትን ሰጥተል፡፡

በተጨማሪም በተቻለ መጠን አጽራረ ቤተ ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያንን እንዳይደፍሩና እንዳያፈርሱ በማእከላት ሥር ያሉ አባላት ከፍተኛ ድርሻ አላቸው፡፡ የማእከላት ልጆች ከሌሎች የቤተ ክርስቲያን አባቶች ጋር በጋራ በመሆን ቤተ ክርስቲያንን ሊያፈርሱ ከሚመጡ ተሕድሶ መናፍቃን፣ አክራሪ እስላሞችና ሌሎች ኃይሎች ጋር ተፋልመው ነው የቤተ ክርስቲያንን ክብርና መብት የሚያስጠብቁት፡፡ ስለሆነም ማእከላት የቤተ ክርስቲያን ክብርና መብት እንዲጠበቅ ከፍተኛ የሆነ ሃይማኖታዊ ተጋድሎ እያደረጉ ያሉ ናቸው፡፡ ከዚህ ባሻገር ቤተ ክርስቲያን ከሀገር ውስጥ እስከ ውጭ ሃገር ዘመኑን የዋጀ አገልግሎት እንድትሰጥና ምእመናንም የተሻለ መንፈሳዊ አገልግሎት እንዲያገኙ ከማድረግ አኳያ የማእከላት ድርሻ የማይተካ ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እስከ ውጭ ሀገራት ድረስ ተደራሽ በማድጋቸውም የውጭ ሀገር ዜጎች የተጠምቀው የሥላሴ ልጅነትን ከማግኘታቸው በተጨማሪ በርካታ የውጭ ሀገር ዜጎች መንፋሳዊ ትምህርት ተምረው ዲያቆናት፣ካህናትና መምህራን ሆነው ቤተ ክርስቲያንን እንዲያገለግሉ ያደረጉት በውጭ ሀገራት የሚገኙ ማእከላት ናቸው፡፡

ይህ ሥራ በቂ ነው ማለት ባይቻለም በተለይ በውጭ ሀገራት የሚገኙ ማአእከላት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ በመላው ዓለም እንዲሰፋፉ የተሻለ አፈጻጸም ማስመዝገብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- እንደ አጠቃላይ ማእከላት መሥራት የሚጠበቅባቸውን ያህል ሠርተዋል ማለት ይቻላል? አገልግሎታቸውስ ዘመኑን የዋጀ ነው ማለት ያስችላል?**

**ዲያቆን አስቻለሁ ጥላሁን፡-** በተወሰነ ደረጃ ማእከላት የሚጠበቅባቸውን ያህል ቤተ ክርስቲያንን እገለገሉ እንደሆነ ይሰማኛል፡፡ ጉድለት ወይም የሚቀራቸው ነገር የለም ብሎ ለመናገር ግን አያስደፍርም፡፡ ጉድለቶች ክፍተቶች ይኖራሉ ነገር ግን ሁሉም ማእከላት የአሠራር ክፍተቶች በተቻለ መጠን በመሸፈን ዘመኑን የዋጀ አገልግሎት ለመፈጸም ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ አሠራር፣አካሄድና ትኩረት ማድረግ ካለባቸው ጉዳዮች አንጻር ደግሞ ማእከላት ገና ብዙ መንገድ መጓዝ ይኖርባቸዋል፡፡ አገልግሎታቸውን ዘመኑን የዋጀ ለማድረግ ጥረት የሚደረጉ ሲሆን በማእከላት የአገልግሎት አፈጻጸም ዙሪያ አንዱ ከሌላው በአፈጻጸም ውጤት ሊለያይ ይችላል፡፡ አጠቃላይ በአገልግሎት ላይ ያለው ጅምር መልካም ቢሆንም ጅምሩን ለማስቀጠልና የተሻለ አገልግሎት አፈጻጸም እንዲኖር ከመሥራት አንጻር በሁሉም መዋቅር ላይ ያሉ ሁሉ ድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- የማእከላት አቅም ግንባታና አባላት አገልግሎት ማስተባበሪያ ክፍል እያከናወነ ያለው ተግባራት ምንድን ናቸው?**

**ዲያቆን አስቻለሁ ጥላሁን፡-** የእኛ ክፍል እየሠራ ያለው በዋናነት የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገራት ማእከላትን መዋቅር መምራት ነው፡፡ ይህ ሲባል ማእከላትን የሚመሩ ሥራ አስፈጻሚዎችን አቅም የማሳደግ ሥራ እንሠራለን፡፡ የገንዘብ፣

የቁሳቁስና የሐሳብ ድጋፍ ሲያስፈልግ ማእከላትን እንደግፋለን፡፡ ከፍተኛ ሁለንተናዊ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ማእከላትን በከፍተኛ ደረጃ እየደገፍን ነው፡፡ አባላት ወደ አገልግሎት እንዲቀርቡና በአገልግሎታቸው እንዲተጉ የመድረግ ሥራ እንሠራለን፡፡ የአባላትን መረጃ ከመያዝ ጀምሮ በአገልግሎት ላይ የማሰማራት ሥራዎችን እንሠራለን፡፡ የማኅበረ ቅዱሳን የተለያዩ የአሠራር መመሪያዎች ተግባሪዊ እንዲሆኑ እንደግፋለን፤ አቅጣጫ እናሳያለን፡፡ በተጨማሪም ዕቅድ አቅደን ማእከላት እርስ በርሳቸው እንዲደጋገፉ እንሠራለን፡፡

እንዲሁም ማእከላት የአገልግሎት ልምድ እንዲጋሩ እናደርጋለን፡፡ የአቅም ማሳደጊያ ሥልጠናዎች፣ ውይይቶችና የማእከላት ቅኝቶች ይደረጋሉ፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- ማእከላት ዘመኑን የዋጀ አገልግሎት እንዲፈጽሙ ተለዋዋጭ የሆነውን የሀገሪቱን ሁኔታ ለማእከላት የምታስረዱበት መንገድ ምንድ ነው?**

**ዲያቆን አስቻለሁ ጥላሁን፡-** የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ ለማእከላት ከምናስረዳበት መንገድ አንዱ ተከታታይ ሥልጠና ሲሆኑ ከሥልጠናው በተጨማሪም በቀጥታ የበይነ መረብ ውይይቶች በማድረግ፣የአካል ቅኝት በማድረግና በተለያዩ ጊዜያት በሚኖሩ የጋራ መድረኮችን እንጠቀማለን፡፡ የተለየና ድንገተኛ ነገር ከተከሰተ በጉዳዩ ዙሪያ ፈጣን የሆነ አቅጣጫ ለማእከላት ይሰጣል፡፡ ጉዳዩን በትክክል እንዲረዱና አገልግሎታቸውም ጉዳዩን ያገናዘበ እንዲሆን መመሪያ እንሰጣለን፡፡ ለማእከላት የምንሰጠው አቅጣጫ እንደ ሁኔታውና እንደአካባቢው ይለያያል፡፡ ለቤተ ክርስቲያንና ለምእመናን ሁልጊዜ የስጋት ቀጠና ለሆኑ አካባቢዎች ቅድሚያ በመስጠት ተከታታይና ልዩ ድጋፍና ክትትል እናደርግላቸዋለን፡፡ እነዚህ ልዩ ድጋፍ በሚፈልጉ አካባቢዎች ለሚገኙ ማእከላት አቅጣጫ የመሥጠት፣የመከታተል ሥራ፣ በሚያጋጥማቸው ችግር ላይ መውሰድ ስላለባቸው ርምጃ የማሳወቅ ሥራዎችን እንሠራለን፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በመጨረሻ በማእከላት ላይ በቀጣይ ምን የተለየ ነገር ለመሥራት ታስቧል?**

**ዲያቆን አስቻለሁ ጥላሁን፡-** በቀጣይ የአባላትን ቁጥር መጨመርና የአገልግሎት አቅማቸውን ማሳድግ ላይ ትኩረት አድርገን የምንሠራ ይሆናል፡፡ የአባላትን መረጃ በተገቢ መንገድ ከመያዝ አንስቶ አባላት በስፋትና በጥረት በአገልግሎት ላይ እንዲሳተፉ የማድረግ ሥራ እንሠራለን፡፡ ሌላው ማእከላትን የማስፈጸም አቅም መገንባት ትልቅ የትኩረት አቅታጫችን ነው፡፡ ማእከላት አመራሮች የመምራት አቅማቸው እንዲያድግ እናደርጋለን፡፡ ምቹና የተሟላ የአገልግሎት ቦታ እንዲኖራቸው ከማድረግ አኳያም ሰፊ ሥራ የሚሠራ ይሆናል፡፡ በግዢ፣ በክራይም ሆነ በሥጦታ የሚገኝን የአገልግሎት ቦታ የተሻለ እንዲሆን ጥረት እናደርጋለን፡፡ የማእከላትን አሁናዊ ችግሮች መፍታት ሌላው የወደፊት ትኩረት አቅጣጫችን ነው፡፡ ማእከላት ችግሮች ከቦታ ቦታ ይለያያልና ያጋጠሟቸውን ችግሮች እየለየን እንደ ማእከላቱ ነባራዊ ሁኔታ የምንፈታ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም በስጋት ቀጠና ላይ ላሉ ማእከላት የምናደርገውን በጥናት የተደገፈ ልዩ ድጋፍ አጠናክረን እንቀጥላለን፡፡


**ስምዐ ጽድቅ፡- ለነበረን ቆይታ እግዚአብሔር ይስጥልን፡፡**

**ዲያቆን አስቻለሁ ጥላሁን፡-** እኔም ስለ ማእከላት የማውቀውን እንድናገር ስለጋበዛችሁኝ በእግዚአብሔር ስም አመሰግናለሁ፡፡

# የቤተ ክርስቲያን ሐኪም ቅዱስ አትናቴዎስ

እህተ ሚካኤል

ልጆች! እንዴት ከረማችሁ! እግዚአብሔር ይመስገን! ለወጆች! አዲሱን ዓመት እንዴት ተቀበላችሁት? መልካም ሰብዕና እንዲኖራችሁ፣ ለወላጆቻችሁ ብሎም ለታላላቆቻችሁ ታዛዥ ተወዳጅ ልጆች ለመሆን በአጠቃላይ ከአምናው የተሻሉ ልጆች ለመሆን አቅዳችኋል? ይህን እየተገበራችሁ ካላችሁ በጣም ጥሩ ነው፡ ፡ ትምህርታችሁንስ እየተከታተላችሁ ነው? አዎን ገና ከአሁኑ ከሥር ከሥር እያጠናችሁ ጥሩ ውጤት ማምጣት ይጠበቅባችኋል፡፡ በቤተ ክርስቲያን፣ በሰንበት ት/ቤት ያላችሁ ተሳትፎ



ቅዱስ አትናቴዎስ

እንዴት ነው? በመንፈሳዊ ሕይወታችሁ በርቱ እሺ ልጆች! ጎበዞች!

ልጆች! ዛሬ መስከረም ፴ የስደቱ መታሰቢያ ስለሆነው በተለይም ‹‹የቤተ ክርስቲያን ሐኪም›› ተብሎ ስለሚጠራው ስለታላቁ ሐዋርያ ስለ ቅዱስ አትናቴዎስ እንነግራችኋለንና በጥሞና ተከታተሉን፡፡

ልጆች! ቅዱስ አትናቴዎስ በ፫፻ ዓ.ም አካባቢ እስክንድርያ ግብፅ ውስጥ ነው የተወለደው፡፡ ወላጆቹ እግዚአብሔርን የማያውቁ አረማውያን ስለነበሩ ስለ ክርስትና ምንም አያውቅም ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ሕፃኑ አትናቴዎስ ሊጫወት ከቤቱ ሲወጣ ጎረቤቶቹ የሆኑ የክርስቲያን ልጆች ሃይማኖታዊ ጨዋታ ሲጫወቱ ተመለከተና ‹‹ክርስቲያን ልሁንና አጫውቱኝ›› አላቸው፡፡ ልጆቹም እሺ አሉትና ዕጣ ተጣጣሉ፡፡ ለአንዱ ቄስ፣ ለአንዱ ዲያቆን ዕጣ ደረሳቸው፡፡ ለሕፃኑ አትናቴዎስም ፓትርያርክ የመሆን ዕጣ ደረሰው፡፡ በዚህን ጊዜ ሌሎቹ ሕፃናት ለአትናቴዎስ ይሰግዱለት ጀመር፡፡

ይህንየሕፃናቱንመንፈሳዊጨዋታየእስክንድርያው ፓትርያርክ ቅዱስ እለ እስክንድሮስ ሰገነቱ ላይ ሆኖ ይመለከት ነበርና ሕፃኑ አትናቴዎስ ወደፊት ትልቅ የቤተ ክርስቲያን አባት እንደሚሆን ትንቢት ተናገረለት፡፡ የአትናቴዎስ አባቱ ሲሞትም እለ እስክንድሮስ ሕፃኑን ከእናቱ ተቀብሎ አጥምቆትና መንፈሳዊ ትምህርት አስተምሮት የዲቁና መዓረግን ሾመው፡፡ ወዲያውም የክርስትና ትምህርትን እንዲያስተምር አዘዘው፡፡ ሕፃኑ አትናቴዎስ ሲያስተምር ብዙ ሰዎች በአንደበቱ ጣፋጭነት፣ በትምህርቱ ይደነቁ ነበር፡፡ እለ እስክምድሮስም ፀጋ እግዚአብሔር በሕፃኑ ላይ ስላደረ ሊቀ ዲያቆን አድርጎ ሾመው፡፡

ልጆች! ቅዱስ አትናቴዎስ ሊቀ ዲያቆናት ሆኖ በተሾመበት ጊዜ መናፍቁ አርዮስ ‹‹ ወልድ ፍጡር ነው›› የሚል የምንፍቅና ትምህርትን በማስተማሩ

በቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ተደርጎ አርዮስን ለማውገዝ ፫፻፲፰ ሊቃውንት ተሰብስበው ነበርና የጉባኤው ጸሐፊ አድርገው ቅዱስ አትናቴዎስን ሾሙት፡፡ ቅዱስ አትናቴዎስም በጉባኤው ላይ መናፈቁ አርዮስን ተከራክሮ አሸነፈው፡፡ ከሌሎች ሊቃውንት አባቶች ጋር በመሆንም የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት በዐደባባይ በመመስከር አርዮስን አሸነፈው፡፡ አርዮስን ተከራክሮ ከመርታቱም በላይ ጸሎተ ሃይማኖትን ያረቀቀው ቅዱስ አትናቴዎስ ነው፡፡

ልጆች! የእስክንድርያው ፲፱ኛ ፓትርያርክ እለ እስክንድሮስ በሕይወት በነበረበት ጊዜ ቅዱስ አትናቴዎስ ከእርሱ በኋላ በእስክንድርያ መንበር እርሱን ተክቶ ፓትርያርክ እንዲሆን ለሕዝቡ ነግሮ ነበርና ፓትርያርክ እለ እስክንድሮስ ባረፈ ጊዜ ሕዝቡ ቅዱስ አትናቴዎስን ሊሾሙት ወሰኑ እርሱ ግን ‹‹እኔ ለዚህ ክብር የምበቃ አይደለሁም›› ብሎ በተራራ ሥር ተደበቀ፡፡ ሕዝቡም ከተደበቀበት ፈልገው አምጥተው በ፴፫ ዓመቱ በ፫፻፳፰ ዓ.ም የእስክንድርያ !ኛ ፓትርያርክ ሆኖ ተሾመ፡፡ ልጆች! ቅዱስ አትናቴዎስ ከቅዱስ እንጦንስ ምንኩስናን የተቀበለ የመጀመሪያው ፓትርያርክ ነው፡፡ ቅዱስ አትናቴዎስ ለ፵፰ ዓመታት ቤተ ክርስቲያንን ያገለገለ ታላቅ አባት ነው፡፡

ልጆች! ቅዱስ ፍሬምናጦስ በ፫፻፳፰ ዓ.ም ለኢትዮጵያ ፓትርያርክ ይሾምላት ዘንድ ለመጠየቅ ከኢትዮጵያ ወደ እስክንድርያ ተልኮ ሄዶ ነበር፡፡ ቅዱስ ፍሬምናጦስ እዚያ ሲደርስ ፲፱ኛው የእስክንድርያ ፓትርያርክ እለ እስክንድሮስ አርፎ በምትኩ ቅዱስ አትናቴዎስ ተተክቶ ስለነበር የመጣበትን ጉዳይ ለፓትርያርኩ አቀረበ፡፡ ቅዱስ አትናቴዎስም ቅዱስ ፍሬምናጦስ በጠየቀው ነገር እጅግ በመደሰት ‹‹ለኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ቋንቋቸውንና ባህላቸውን የሚያውቅ ከአንተ በላይ ማንም የለም›› በማለት ቅዱስ ፍሬምናጦስ ራሱን የኢትዮጵያ ጳጳስ አድርጎ በመሾም ወደ ኢትዮጵያ መልሶታል፡፡

ልጆች! ቅዱስ አትናቴዎስ በሕይወት ዘመኑ ስለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ብዙ መከራዎችን ተቀብሏል፡፡ የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች ለ፭ ጊዜ ከመንበሩ በማፈናቀል ወደ በረሃ እንዲሰደድ አድርገውታል፡፡ ለ፲፭ ዓመታት ያህልም በስደት አሳልፏል፡፡ ቅዱስ አትናቴዎስ ግን በተሰደደባቸው ቦታዎች ሁሉ መከራን እየተቀበለ ያላመኑትን ስለክርስቶስ በማስተማር ክርስቲያን ሲያደርግ ኖሯል፡፡ ከሩቅ ላሉት ደግሞ የማጽናኛ መልእክቶችን በመጻፍ ክርስቲያኖች በሃይማኖታቸው እንዲጸኑ፣ ሃይማኖታቸውን እንዲጠብቁ ሲመክር ዘመኑን አሳልፏል፡፡ በቤተ ክርስቲያን የሚነበበው ሃይማኖተ አበው የተጻፈው በቅዱስ አትናቴዎስ ዘመን ነው፡፡

ልጆች! ቅዱስ አትናቴዎስ በኖረበት ዘመን ሁሉ ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት የሚነሱ አረጋውያንን ሲታገል የኖረ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን አርበኛና ጠበቃ ነው፡፡ ይህ ቅዱስ አባት በሕይወት ዘመኑ ብዙ መንፈሳዊ ሥራዎችን በመስራት፣ ታላላቅ ተጋድሎዎችን በመጋደል ቤተ ክርስቲያንን ከብዙ ጥቃት ተከላክሏል፡፡ ቅዱስ አትናቴዎስ እጅግ ሲበዛ ሃይማኖተኛ እና ለእምነቱ ቀናኢ ነበር፡፡ ጀግና፣ ዘዴኛ፣ ትሁት አባትና ጥበብን የተሞላ ጻድቅ ነበር፡፡ ቅዱስ አትናቴዎስ በሕይወት ዘመኑ ብዙና ታላላቅ ሃይማኖታዊ ሥራዎችን ሠርቶ፣ በ፸፭ ዓመቱ አርፏል፡፡ ቅደስት ቤተ ክርስቲያን ይህን አባት ‹‹ሊቀ ሊቃውንት››፣ ‹‹ርዕሰ ሊቃውንት››፣ ‹‹የቤተ ክርስቲያን ሐኪም››፣ የሕይወት ምንጭ›› በማለት ትጠራዋለች፡፡

ልጆች! መስከረም ፴ ሐዋርያው ቅዱስ አትናቴዎስን የስደቱ መታሰቢያ፤ ከስደቱ የተመለሰባት ቀን ናትና ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ይህችን ዕለት ታከብራለች፡፡

ልጆች! በሚቀጥለው ጊዜ በሌላ ታሪክ እስክንገናኝ ቸር ቆዩ!

የቅዱስ አትናቴዎስ በረከቱ ይደርብን አሜን!

**ምንጭ**

ቅዱስ አትናቴዎስ ሕይወቱ እና ትምህርቱ
የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ

# ከመባቻ እስከ መካተቻ

ኪኑኪሩ ከአዲስ አበባ

እግዚአብሔር በሠራው ፍጥረት መታደስን፣ተስፋና ብርሃንን እናያለን፡፡ የዚህ ምስክሩ የአዲስ ዓመት መባቻ ተፈጥሮ የምታሳየን የመታደስ ገጽታ ነው፡፡ የተፈጥሮ መታደስ ሀብትን፣ ውበትን፣ ርካታን፣ ዕድልን ለመጨመር ነው፡፡ ለሚሠራበት በትናንቱ ላይ የሚጨምርበት፣ ከትናንት በተሻለ ከፍ ከፍ የሚልበት ጸጋ ማግኘት ነው፡፡

ሰዎች የተሰጣቸውን የተፈጥሮ ጸጋ በውል መጠቀም ይገባቸዋል፡፡ የተፈጥሮ አዲስነት በራሱ ለሰዎች አዲስና ብሩህ ነገር እንዲያስቡ ገፊ ምክንያት ይሆናቸዋል፡፡ ራሳቸውን ይጠይቃሉ፡፡ ለምን እኔስ አልታደስም፣ አላንሠራራም፣ አልሻሻልም ይላሉ፡፡ ከተፈጥሮ አዲስነት ጋር ራሳቸውን አብረው ለማራመድ ይጥራሉ፡፡ ስለዚህም ብሩህ ሐሳብ ስለሚይዙ በዓመቱ መባቻ ላይ በተነሣሽነት መንፈስ ይራመዳሉ፡፡

ይህ በክርስቲያኖችም ሕይወት ዓመቱን ለንስሓ፣ ለመንፈሳዊ ፍሬ ማፍሪያ፣ ለበጎነት መንደርደሪያ ያደርጉታል፡፡ ለብርቱዎች በትናንት ላይ ለመጨመር፣ ከትሩፋት ወደ ትሩፋት ለማደግ ያልሙበታል፡፡ ለደካሞች ከትናንት ራስን አጠንክሮ ለመራመድ ያቅዱበታል፡፡

ይሁን እንጂ ትልቁ ጭንቅ በዓመቱ መጀመሪያ ሳይሆን ቀናት ቀናትን እየወለዱ፣ ወራትም ወራትን እያስከተሉ ሲነጉዱ በመንፈቀ ዓመት ማነከስና መሰልቸት፣ አለመጽናትና መንገዳገድ የሚከበን ሰዎች ራሳችንን እንታዘባለን፣ ሌሎችም ይታዘቡናል፡፡

በመባቻ የያዝነውን መነቃቃት በመካተቻ እንጥለዋለን፡፡ የጀመርነውን አንጨርስም፡፡ በዚህ ጊዜ መዛልና መውደቅ ይከተላል፡፡

ሕይወቱን በንስሓ የጀመረ ሰው መልሶ ወደ ኃጢአት ጎዳና ካዘነበለ፣ የተጸጸተበትን ነገር መልሶ ካደረገ፣ ሲጀመር የታጠበ ሰው መልሶ ከጨቀየ ‹‹ውሻ ወደ ትፋቱ ይመለሳል፥ ደግሞ፦ የታጠበች እሪያ በጭቃ ለመንከባለል ትመለሳለች እንደሚባል እውነተኞች ምሳሌዎች ይሆንባቸዋል፡፡›› እንዳለው ይሆናል፡፡ (፪ኛ ጴጥ ፪፥፳፪)

ሕይወታቸውን በጾም በጸሎት ለመምራት ወስነው መስከረም ላይ የጀመሩ ሰዎች ጥቅምትና ኅዳር ሲታክቱ ቢገኙ መጀመሪያ በራሳቸው ፊት ትዝብት ላይ ሲወድቁ ይታያሉ፡፡ ከዚያ ሌሎች መጀመራቸውን ያስተዋሉ ሰዎች መታዘብ ይቀጥላሉ፡፡

መስከረም ወር ላይ ቃለ እግዚአብሔርን ለመስማት በየጉባኤው የሚታደሙ በየዓውደ ምሕረቱ የሚያዘወትሩ ሰዎች ወራት ሲቆጠሩ ከዕለት ዕለት እየረሷቸው ጭራሹኑ እስከ መተው ሲደርሱ ቢታዩም እንዲሁ ነው፡፡ ከራሳቸው ጀምሮ ያያቸው ሁሉ ይታዘባቸዋል፡፡ ከመታዘብ አልፎ ግን የሚሰናከልባቸውም ይኖራል፡፡

ቅዱሳት መጻሕፍትን ለማንበብ፣ ገዳማትን ለመሳለም፣ አብያተ ክርስቲያናትን ለማገልገል በመጀመሪያዎቹ ወራት የተነሣሡ ሰዎች ሲቆዩ ከራሳቸው ጋር የገቡትን ቃል ሲያፈርሱ ሊስተዋል ይችላል፡፡ ይህ በብዙዎቻችን ሕይወት ውስጥ ሊንጸባረቅ ይችላል፡፡ አለመጽናታችን ግን በራሳችን በሰውም በእግዚአብሔርም ፊት ግን ደስ የማያሰኝ ይሆንብናል፡፡

ለሰዎች መልካም ለማድረግ፣ የበጎ አድራጎት ሥራዎችን ለመሥራት በመስከረም የተነሣሡ ሰዎች ከወራት በኋላ ሰው የሚጠሉ ቁጡና ተሳዳቢ ሆነው ቢገኙ ትዝብት ላይ ይወድቃሉ፡፡ ‹‹የቀደመ ፍቅርህን አትተው›› እንዲል መጽሐፍ ለሰውም ሆነ ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር ማጽናት ከክርስቲያን በብርቱ ይፈለጋል፡፡ ጀምረን ሳለን መሐል ላይ ማነከስ ያሳዝናል፡፡

ጅማሬያችን ከልብ ሲሆን ፍጻሜያችንም እንዲሁ ይሆናል፡፡ መነሣሣታችን ከስሜት የጸዳ መሆን አለበት፡፡ ‹‹በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ፡፡›› (ሮሜ. ፲፪፥፪) ያለው የመጽሐፍ ቃል መደገፊያ ሊሆነን ይገባል፡፡ ስሜታዊ ሆነን ስንጀምር የቆምን ሊመስለን ይችላል፤ መዛልና መብረክረኩ መፈተኑ የሚመጣው ውለን ስናድር ነው፡፡ የጽናት ጉዳይ የሚመጣው በመጨረሻዎቹ ወራት ነው፡፡

ለአንዳንዶች ግን ራሳቸውን እስኪታዘቡ የሚያደርሳቸው በመስከረም የቆሙ መስሏቸው ሳለ ከወራት በኋላ ወድቀው መገኘታቸው ነው፡፡ የትዕግሥታችን ፍሬ ጣፋጭ ሲሆን የሚችለው መጨረሻ ላይ ነው፡፡ ከወራት ወራት የምንራመደው በትዕግሥት መሆን አለበት፡፡ ቆመን መጽናታችንን የምናወድሰው እግዚአብሔርንም የምናመሰግንበት አዲስ ብለን ጀምረን የያዝነውን ነገር ጳጉሜን ድረስ ይዘን ተጉዘን ለተጨማሪ ጸጋና ትሩፋት አዲስ ብለን መጀመራችንን ስናረጋግጥ ነው፡፡ እንዲህ ሲሆን በአዲስ ዓመት ከፍ ላለ ተጋድሎና በተጋድሎም ለሚገኝ ከፍ ላለ ጸጋ ተነሣሥተናልና አዲስ ሕይወት እንጀምራለን፡፡ የያዝነው ነገር ሲዘልቅልን፣ አዲስ እንደሆነ ሲቀጥል በእጅጉ ያስደስታል፤ መጽሐፍ

እንዲህ እንዳለ ‹‹በእነዚህ አርባ ዓመታት የለበስኸው ልብስ አላረጀም፥ እግርህም አላበጠም።›› (ዘዳ ፰፥፬)

አዲስ መሆንን ማስቀጠል የምንችለው በጽናት ነው፡፡ ዓመት ብዙ ዕለታት አሉት፡፡ በእነዚያ ዕለታት ብዙ ነገሮች ይፈራረቃሉ፡፡ በእነዚህ ለውጦች ውስጥ ደግሞ መፈተን ይኖራል፡፡ በእነዚህ ፈተናዎች ፊት መጽናት ደግሞ በአዲስ ዓመት መባቻ ለማድረግ የጀመርነውን እስከ መካተቻ ይዘን እንድንቀጥል ያስችላል፡፡ በጎን ነገር አጽንተን መቀጠል የምንችለው ደግሞ በእግዚአብሔር ረድኤት ነው፡፡ በእርሱ ተመክተን መጀመር ለፍጻሜ ያበቃል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም ‹‹በበጎ ሥራ በመጽናት ምስጋናንና ክብርን የማይጠፋንም ሕይወት ለሚፈልጉ የዘለዓለም ሕይወት ይሰጣቸዋል፤›› (ሮሜ ፪፥፯) ያለውን ቃል ማሰብ ይገባናል፡፡ ለደቀ መዝሙሩም ‹‹በጊዜውም አለጊዜውም ጽና፥›› (፪ኛ ጢሞ ፬፥፪) ማለቱ በጊዜያት ውስጥ በሚመጡ ልዩ ልዩ ሁኔታዎች ውስጥ ከእኛ የሚፈለግ በደረጃ ላቅ ያለ ጽናት አለ ማለት ነው፡፡

ሰዎች ለራሳችን ባልታመንን ቁጥር ራሳችንን እንጠላለን፡፡ ራሳችንን ደጋግመን በትዝብት ዓይን ካየነው ውስጣችን ይቃወሳል፡፡ ሰው ራሱን የመምራት ችግር እንዳጋጠመው ካሰበ ራሱን የሌላ አድርጎ ስለሚቆጥር ተስፋም ሊቆርጥ ይችላል፡፡ የዚህ መፈተኛው ደግሞ በጊዜያት ውስጥ እናደርገዋለን ያልነውን ነገር ባሰብነው ጊዜ መፈጸም አለመቻል አንዱ ነው፡፡ ይህ ራስን ከመግዛት ጋርም ይገናኛል፡፡ ‹‹በበጎነትም ዕውቀትን ፥ በዕውቀትም ራስን መግዛት፥ ራስንም በመግዛት መጽናትን፥ በመጽናትም እግዚአብሔርን መምሰል፥›› የሚለው የሐዋርያው ቃል (፪ኛ ጴጥ ፩፥፯) ይህንን ያሳስባል፡፡

የጀመርነውን መፈጸም በሂደት አለመጽናት የሚወለደው ስሜታዊ ሆኖ ከመመላለስ ነው፡፡ ያለንበትን ጊዜያዊ ሁኔታ ሳይሆን ዘላቂውን በብዙ ለውጦች ውስጥ የማለፋችንን ነገር ካለማሰብ ነው፡፡ ክርስቲያኖች ከትናንት መማር ይገባል፤ ከታላላቆቻችን መማር ይገባል፡፡ ከላይ በዕውቀት ራስን መግዛት ያለው የሐዋርያው ቃል ሊጠበቅ የሚችለው ከትናንት ልምዶቻችን፣ ከታላላቆቻችን፣ ከመጻሕፍትም ስንማር ነው፡፡ ይህ ከስሜት ያድነናል፡፡ መጽሐፍ ‹‹የዱሮውን ዘመን አስብ፥ የብዙ ትውልድንም ዓመታት አስተውል፤ አባትህን ጠይቅ፥ ያስታውቅህማል፤ ሽማግሌዎችህን ጠይቅ፥ ይነግሩህማል።›› (ዘዳ ፴፪፥፯) ያለውን እንደትጥቅ መያዝ ይገባል፡፡ በእርግጥም ዕውቀት ከስሜት ያወጣል፡፡ ስለዚህ አቅማችንን፣ የሕይወት ዓላማችንን፣ ያለንን ጸጋና ሀብት ከግምት አስገብተን በመስከረም እናቅዳለን፤ ይህ ሲሆን እስከ ጳጉሜን ድረስ በጽናት ያቀድነውን እየፈጸምን እንጓዛለን፡፡

ሌላው የጀመርነውን መፈጸም በሂደት አለመጽናት የሚወለደው በትዕግሥት ለመመላለስ ካለመፍቀድና ካለመዘጋጀት ነው፡፡ ሥጋ ለባሾች ስለሆነን በጎውንም ነገር ለመሰልቸት ልንጋለጥ እንችላለን፡፡ ሥጋ ምንም ያህል ቢመረው ነፍሳችን ልታጣጥመው ለተዘጋጀችበት ጣፋጭ ፍሬ ራሳችንን ወደፊት ማራመድ ያስፈልጋል፡፡ ‹‹በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ፤›› (ዕብ ፲፪÷፩) እንደተባለው ነው፡፡

ሌላው ፈታኝ ሁኔታችን ግን አሁንም ቀን አለኝ ብሎ ከመዘናጋት የሚመጣ ስንፍና ነው፡፡ መስከረም የጀመረ ሰው ጥቅምት ላይ ሰንፎ ሌላ መስከረም ስላለኝ ያን ጊዜ አደርገዋለሁ ብሎ ማሰብ ትዘብት ላይ የሚጥል ነው፡፡ በዚህ ግን ብዙዎች ራሳቸውን ያታልላሉ፡፡ ነገር ግን ሁሉም ዓመት ለሰዎች ምቹ አይሆኑም፤ ‹‹ነገ›› ብሎ መቅጠር የሚገባ አይሆንም ፤ የተሰጠንን ዘመን መጠቀም እንጂ፡፡ ‹‹ነገ›› ምን አልባትም ያቀድነውን ሁሉ ልንፈጽም የማንችልበት የከፋ ዘመን ሊሆን ይችላል፡፡ ጠቢቡ ሰሎሞን ‹‹የጭንቀት ቀን ሳይመጣ በጕብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ፤ ደስ አያሰኙም የምትላቸውም ዓመታት ሳይደርሱ፤›› (መክ ፲፪፥፩ ) ያለው ይህንን ዓይነት ስንፍና ለመዋጋት ነው፡፡

ይህ አስተሳሳብ ግን በእጅጉ የሚነቀፈው በሌለን ሥልጣን ነገን እንደምንኖርበት ማሳባችንም ነው፡፡ የተሰጠንን ሳንጠቀም ሌላ አዲስ ዓመትና መስከረም እንደሚመጣ አስበን መዘናጋት፣ የጀመርነውን ማቋረጥ አስተዛዛቢ ነው፡፡ ሐዋርያው ‹‹ዛሬ ወይም ነገ ወደዚህ ከተማ እንሄዳለን፤ በዚያም ዓመት እንኖራለን እንነግድማለን እናተርፍማለን የምትሉ እናንተ፥ ተመልከቱ፥ ነገ የሚሆነውን አታውቁምና፡፡ ሕይወታችሁ ምንድር ነው? ጥቂት ጊዜ ታይቶ ኋላ እንደሚጠፋ እንፍዋሎት ናችሁና፡፡ በዚህ ፈንታ ጌታ ቢፈቅድ ብንኖርም ይህን ወይም ያን እናደርጋለን ማለት ይገባችኋል።›› ያለው ይህን መሰል ስሜት ያላቸውን ሰዎች ሲመክር ነው፡፡ (ያዕቆ ፬፥ ፲፫)

ስለዚህ ክርስቲያኖች ሆነን ሳለን በዕውቀት ሳይሆን በስሜት፣ በትሕትና ሳይሆን በትዕቢት፣ በትዕግሥት ሳይሆን በመታከት፣ ራስን በመግዛት ሳይሆን በመደዴነት ከተጓዝን አዲስ ዓመት ያሰብነውን ያህል አዲስ አይሆንልንም፡፡ በአዲስ ዓመት መባቻ በብሩህ መንፈስ የጀመርነው ሁሉ አይቀጥልም፡፡ ይህንን ካላደረግን ደግሞ ራስን ከመታዘብ ጀምሮ በሰውና በእግዚአብሔር ሚዛን ፊት መቅለል ያስከትልብናል፡፡

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

# በሥራ ቦታዬ ካሉ ሰዎች ጋር መስማማት አልቻልኩም

ውድ የስምዐ ጽድቅ አዘጋጆች እንዴት አላችሁ? እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደኅና ነኝ። ስሜ ወለተ ጊዮርጊስ ይባላል። በአንድ ትልቅ የመንግስት መሥሪያ ቤት ውስጥ ሠራተኛ ነኝ። በዚህ መሥሪያ ቤት ውስጥ በዙሪያዬ ባሉ ሰዎች ብዙም ደስተኛ አይደለሁም። በብዙ መልኩ ከተገልጋይ ጋር የሚያገናኝ መሥሪያ ቤት እንደመሆኑ መጠን ብዙ ወንጀልና ግፍ በተገልጋይ ላይ ሢሰራ ሳይ አዝናለሁ። ከበታቼም ሆነ ከበላዬ ያሉና በአጠገቤ ያሉ የሥራ ባልደረቦቼ የሚሠሩትም ሆነ የሚናገሩት ነገር ከሥነ ምግባር የወጣ ነው። በተለይም ከእኔ ክርስቲያናዊ ሕይወትና ተገቢ ነው ብዬ ካመንኩበት አኗኗር በተለይ ደግሞ መሥሪያ ቤቱ ካለው መመሪያ አንፃር በብዙ ነገር ግራ እጋባለሁ። ብዙ ጥፋት ሢሠራ ባይም ዝም እላለሁ እንጂ መጋጨቱን ብዙ አልፈልግም፤ ብዙ ጊዜም መታገሥ እመርጣለሁ። ከተቻለ መሥሪያ ቤቱን ለቅቄ በመሔድ መለየት አስባለሁ፤ ነገር ግን የተሻለ ደሞዝ የሚከፍለኝና ለሙያዬ በእጀጉ የቀረበ መሥሪያ ቤት በመሆኑ ብለቅ በእኔም ሆነ በቤተሰቤ የኑሮ ሁኔታ ላይ ጫና ይፈጥራል። ስለዚህ አንዳንዴ ሲመረኝ ክፉ ደግ ለመነጋገር እገደዳለሁ፤ የሚሠሩት ሥራ ተገቢ አለመሆኑን ጭምር ፊት ለፊት በመናገር ለማሳመን ብሞክርም አልተሳካልኝም። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ከእንደዚህ ዓይነት ሰዎች ጋር እንዴት ሆኜ መቀጠል እችላለሁ ብዬ እጨነቃለሁ። ሕይወቴን በእንደነዚህ ዓይነት ሰዎች መካከል እንዴት መምራት እችላለሁ? ምንስ ማድረግ አለብኝ? የዕናንተን ምክር እሻለሁ።

ውድ ጠያቂያችን! በመጀመሪያ አክብረው ለዓምዳችን በላኩት ጥያቄ ምስጋና እናቀርባለን። እንደሚረዱት ሰዎች ከሚኖሩት የእምነት ሕይወት፣ ካደጉበት አካባቢ ባህልና ሥነ ልቡና ፣ በየጊዜው ባሉ ሁኔታዎች ውስጥ በግል ወይም በጋራ ካሉብን ልዩ ልዩ ዝንባሌና ፍላጎቶች ምክንያት አንዱ ከአንዱ ጋር የሚስማማባቸው ወይም የሚቃረንባቸው ሁኔታዎች ይፈጠራሉ።

ክርስቲያኖች በዚህ በፍላጎትና በዝንባሌ በእምነት የተለያየ ማኅበረሰብ በሚኖርበት ዓለም ውስጥ የሚኖሩ ናቸው። ስለዚህ ከእነዚህ ሁሉ ጋር እንዴት እንደሚኖሩ ክርስቲያኖች እንዲጠበቡ ያስፈልጋል። ይህ ዓለም ክፋትና መከራ ያለበት ዓለም ነው። ‹‹እነሆ፥ እኔ እንደ በጎች በተኵላዎች መካከል እልካችኋለሁ፤ ስለዚህ እንደ እባብ ልባሞች እንደ ርግብም የዋሆች ሁኑ።››ብሎ ጌታችን ሲናገር የክርስቲያኖች መንገድ አስጨናቂ መሆኑን እናስተውላለን።(ማቴ፲፥፲፮)

በዓለም ውስጥ ሁሉም ሰው ክርስቲያናዊ የእምነት ሕይወት፣ አመለካከትና አኗኗር ሊኖረው አይችልም። ስለዚህ ሕይወትን የምንኖረው ከአስቸጋሪ ሰዎችም ጋር ነው። ይህ ማለት ግን አስቸጋሪ ሰዎች ስለሆኑ አንድናስቆጣቸው፣ እንድናወግዛቸው፣ እንድናገላቸው የተፈረደባቸው ናቸው ማለት ሳይሆን ልናገለግላቸውም ኃላፊነት ይዘን አብረውን እንዲኖሩ እንፈቅዳለን ማለትም ነው።

‹‹ለማንም ስለ ክፉ ፈንታ ክፉን አትመልሱ፤ በሰው ሁሉ ፊት መልካም የሆነውን አስቡ። ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ።›› (ሮሜ ፲፪፥ ፲፰) የሚለው የሐዋርያውን የምክር ቃል ገንዘብ ማድረግ ነው። ከሰዎች ጋር መኖር ማለት ደግሞ ከክርስቲያን ማኅበረሰብ ጋር፣ ቤተሰባችን ጋር፣ ከጎረቤቶቻችን ጋር፣ ከሥራ ባልደረቦቻችን ጋር፣ እንደ ሀገር ከሀገራችን ዜጎች ሁሉ ጋር፣ ከዓለሙም ሁሉ ሕዝብ ጋር ማለታችን ነው።

ከቤተሰባችን ጋር ጋብቻ፣ የመዋለድ፣ የዝምድና ሕግን ጠብቀን መኖር ማለት ነው። ከጎረቤቶቻችን ጋር የመንደሮቻችንን የጋራ ማኅበራዊ፣ ባህላዊ፣ አስተዳደራዊ ወዘተ ሕግ ጠብቀን ማለታችን ነው። በሥራ ቦታችን አሠሪና ሠራተኞች፣ ሥራና ሠራተኛን፣ ሠራተኛና ተገልጋይን፣ሠራተኛና ሠራተኛን ወዘተ በሚያስተሳስሩ ሕግና መመሪያዎች እየተገዛን ማለት ነው። በሀገር ደረጃም የሀገርን ሕግ፣ በዓለም ውስጥም ሰብአዊና ዓለም አቀፍ ሕግጋትን ጠብቆ መኖር ማለታችን ነው። በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን የማይገሰሰው ክርስቲያናዊ ሕግጋት ሳይሸራረፉብን እንዲሆን ተጋድሎ እናደርጋለን።

ውድ ጠያቂያችን! ያጋጠመዎትን በሥራ ቦታ የሚያጋጥም የግንኙነት ችግር መፍትሔ ለመስጠት ወይም አቋም ለመያዝ ተቋማዊ ሕግጋትንና ክርስቲያናዊ ሕይወትን መነሻ አድርጎ በየቅጽበቱ መራመድን ይሻል።

ከምንም በላይ ግን ግንኙነትን የሠመረና ተገቢ ለማድረግ ራስን ማወቅ አስፈላጊ ነው። ራስን በመጀመሪያ መመርመር ግድ ነው። በራስ ማንነት፣ሐሳብና ተግባር ላይ ዕውቀት ሊኖረን ይገባል። ሰዎች አልተመቹኝም ከማለት በፊት እኔ ምን ያህል ትክክለኛ፣ ቅን፣ ታማኝና የፍቅር ሰው ነኝ ወይ ብሎ ራስን መመርመር ያስፈልጋል። ሌላው ሰው ላይ ያለን ችግር ለማየት አስቀድሞ ራስን በጠራ ዓይን ማየት ይገባል። ‹‹አስቀድመህ ከዓይንህ ምሰሶውን አውጣ፥ ከዚያም በኋላ ከወንድምህ ዓይን ጉድፉን ታወጣ ዘንድ አጥርተህ ታያለህ።›› በማለት ተጽፏልና (ማቴ ፳፫፥፳፮)

ውድ ጠያቂያችን! አስቀድመው የሥራ ባልደረቦችዎ በእርስዎ ላይ ያላቸውን የቅሬታና የቊጣ ምንጮችን በውል ይለዩ፤ በትጋትና በታማኝነት ሥራዎን አይሠሩ ከሆነ፣ ሥራዎን በብቃት ለመፈጸም የአቅም ውስንነት አጋጥሞዎት ከሆነ፣

ለመምከርና ለማገዝ ሳይሆን ለቊጣ፣ ለነቀፌታና ለክስ የሚቻኮሉ ከሆነ፣ አለአግባብ ጥቅምን የሚያገኙ ከሆነ፣ ሰዎችን በአድልዎ የሚያዩ ከሆነ፣ የተቋሙንና የተቋሙን ማኅበረሰብ ሕግና ደንቦች የማያከብሩ ከሆነ ወዘተ ባልደረቦችዎ ለእርስዎ ባላቸው አመለካካትና ግንኙነት ላይ እንቅፋት ይፈጠራል።

ውድ ጠያቂያችን! እርስዎን ከሚያስነቅፉ ነገሮች ነጻ ሆነው፣ እንደገለጹልንም ክርስቲያናዊ መንፈስን ይዘው የሚመላለሱ ከሆነ ከእርስዎ የሚጠበቀው በባልደረቦችዎ በኩል ለእርስዎ ፈተና የሆኑ ጠባያትን ምንነትና ደረጃ በውል መለየት ነው። እነዚህ ጠባያት በሥራ አካባቢ እንዲዳብሩ ምክንያት የሆነባቸውን መሠረታዊ ነገሮች ማጥናት ነው። ይህንን ሲያደርጉ ግን እነርሱን የሚያዩበትን ዓይን ጤናማ ማድረግ ያስፈልጋል።

ባልንጀሮቻችንን የምናይብት ዓይን ጤናማ የሚሆነው ፍቅር ያልተለየው ሲሆን ነው። ባሳለፏቸው የሥራ ጊዜያት አዋኪ ሆነዋል ብለው ያሰቧቸውን ባልደረቦች በቊጣ፣ በክስ፣ በወቀሳ፣ በምሬት፣ በጠላትነት ወዘተ ከማየትዎት በፊት በርኅራኄ መንፈስ፣ በትዕግሥት መንፈስ፣ በማገልግል መንፈስ ያዩባቸውን ቅጽበቶች ምን ያህል እንደሆነ ገምግሙ። በዚህ መንፈስ አዋኪ ባልደረቦችዎን ባዩባቸው ቅጽበቶች ምን አደረጉ? በጸሎት አስበዋቸው እንደሆነ፣ በምክር ጎብኝተዋቸው እንደሆነ በቃል ወይም በመጽሐፍ ቃለ እግዚአብሔር አገልግለዋቸው እንደሆነ ወዘተ ያስቡ።

ሰዎች ትክክለኛና የለዘቡ ሆነው እንዲቀርቡን ብቻ መጠበቅ የለብንም። ሰዎች ትክክለኛና የለዘቡ እንዲሆኑ ልናገለግላቸውም ይገባል። ለዚህ ደግሞ መጠበብ ያስፈልጋል። ሐዋርያው ‹‹እውነትን በፍቅር እየያዝን በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ፤›› (ኤፌ ፬፥፲፭) እንዳለ እውነትን ለማጽናት ብለን የምንጣላቸው፣ ጦር የምንሰብቅባቸው ባልንጀሮች እንዳይኖሩን መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

በዚህ ረገድ ተግባራችን፣ ቃላችን፣ ገጽታችን ሁሉ በጎ ተጽእኖ ሊፈጠር ይገባል። የሰዎች አልጫ መሆን ሊያበሳጨን አይገባም። ጨው ሆነን ልናጣፍጣቸውም ኃላፊነት አለብን። ልባም መሆን ለክርስቲያን ግዴታው ነው። በዚህ ጊዜ ክፋውን መንፈስ ሁሉ በበጎ እንለውጠዋለን። መጽሐፍም እንዲህ እያለ ይመክረናል።

‹‹የለዘበች መልስ ቊጣን ትመልሳለች፤ ሸካራ ቃል ግን ቊጣን ታስነሣለች።›› (ምሳ. ፲፭፥፩)፤

‹‹በውጭ ባሉቱ ዘንድ በጥበብ ተመላለሱ። ለእያንዳንዱ እንዴት እንድትመልሱ እንደሚገባችሁ ታውቁ ዘንድ ንግግራችሁ ሁልጊዜ፥ በጨው እንደ ተቀመመ፥ በጸጋ ይሁን።›› ቆላ. ፬፥፭) ተብሎ እንደተጻፈ ክርስቲያን የሆነ ሰው ከሌሎች ተሽሎ መግኘት እንዳለብን መገንዘብ ተገቢ ነው። ሰዎች የኛን አርአያ ይከተሉ ዘንድ አሊያም የምንለውን የሰሙ ዘንድ እኛ በነገር ሁሉ ከእነርሱ የተሻልን ሆነን መገኘት ሁሉን በትዕግሥት ማሳለፍና ድካማቸውን ቀስ ብሎ ማስረዳት መልካም ግኑንነት እንዲኖረን ከማድረጉም በላይ የሰዎችን አስቸጋሪ ባሕሪ መቀየር ይቻላል።

ከዚህ አልፎም የሚያስቆጣ የሚያሳዝን ነገርም እያደረጉብን ስለፍቅር ብለን ክፋውን በበጎ እየመለስን ልባቸውን ወደ ቀናው መንገድ ለመመለስ መትጋት አለብን። ይህ በወንጌል ጌታችን ‹‹በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፥ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፥ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፤››(ማቴ ፭፥ ፵፬) በማለት በሰጠን ቃሉ መሠረት የምንጠልፍበት ተጋድሎ ነው።

ውድ ጠያቂያችን! ይህ ማለት ግን ከአቅማችን በላይ የሆነ ነገር አያጋጥመንም ማለት አይደለም። ክፋትን አጽንተው እስከ መጨረሻው ፈተና የሚሆኑብን ሰዎች በሥራ ገበታችን አካባቢ ላይጠፉ ይችላሉ። ይህ ሲሆን ደግሞ በራስ ጥረት፣ በጓደኞች ጥረትና በተቋማዊ አሠራር ተደግፎ ፈተናውን ለማራቅ መትጋት ደግሞ ያስፈልጋል። ይህም ጌታችን በሰጠው በሚከተለው ቃሉ መሠረት ቢሆን የተመረጠ ነው። ‹‹ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱ እንዲጠፋ በሰማያት ያለው አባታችሁ ፈቃድ አይደለም። ወንድምህም ቢበድልህ፥ ሄደህ አንተና እርሱ ብቻችሁን ሆናችሁ ውቀሰው። ቢሰማህ፥ ወንድምህን ገንዘብ አደረግኸው፤ባይሰማህ ግን፥ በሁለት ወይም በሦስት ምስክር አፍ ነገር ሁሉ እንዲጸና፥ ዳግመኛ አንድ ወይም ሁለት ከአንተ ጋር ውሰድ፤ እነርሱንም ባይሰማ፥ ለቤተ ክርስቲያን ንገራት፤ ደግሞም ቤተ ክርስቲያንን ባይሰማት፥ እንደ አረመኔና እንደ ቀራጭ ይሁንልህ።›› ብሏል። (ማቴ ፲፰፥፲፬)

በመሥሪያ ቤት የሚኖሩ ባልደረቦች ክርስቲያኖች ሆኑ ሌሎች በተቻለ መጠን ከላይ በተጠቀሰው መንገድ በበጎ መንፈስ እንዲራመዱና ለመንፈሳዊ ሕይወታችን የተስማማ ስብእና እንዲኖራቸው መትጋት ያስፈልጋል። ከአቅም በላይ ሲሆን ግን በተቻለ መጠን መምከርና መገሠጽ ተገቢ ነው። ግላዊ ምክርና ተግሣጻችንን የማይቀበል(ሉ) ከሆነ ያግባባናል ብለን ከምናምንባቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር ሆኖ መምከር ያስፈልጋል።

ከዚህ ከተሻገረ ደግሞ ወደ አደባባይ ማምጣት ይገባል። አደባባይ የምንለው አስተዳደራዊ ሕግጋት ጉዳዮች የሚታዩበት አሠራር ነው። በዚህም መሠረት የአስተዳደር ሕግጋትን መነሻ አድርገን በሚመለከተው አካል በኩል ጉዳዩን ማቅረብና ፍትሕ መሻት ተገቢ ይሆናል ማለት ነው።

ውድ ጠያቂያችን! እርስዎ ክርስቲያናዊነትን ጠብቀው መራመድዎን ካረጋገጡ በኋላ አንድ ክርስቲያን ለማገልገል የሚሄዱበትን ምዕራፍን አይርሱ። በግልና በጋራ መምከርንና በመጨረሻም ፈተና ለማቅለል የሥራ ባልደረቦችን ፈተና በአስተዳደራዊ እና በሥነ ምግባር ሕግጋት ለማቅልል እንዲተጉ ለመምከር እንወዳለን።

***ወስብሐት ለእግዚአብሔር***